# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ









## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል

ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ




## ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ!

ይህ መጽሓፍ የት/ቤቱ ንብረት ነው፡፡ በጥንቃቄና በእንክብካቤ ይያዙት፡፡

**ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡**

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥ ገጾቹም አለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋንም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና አለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሰርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገጾቹን ደጋግሞ አለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ሥዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማስተሽ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሣ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉ ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገጾቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ
# እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
# የተማሪ መጽሐፍ

5ኛክፍል


**አዘጋጆች፡-**

አሸናፊ ደጉ

በቀለ ሙዳ

ስናፍቅሽ አስፋው

**አርታኢ፡-** ቴዎድሮስ ቦጋለ(ኤም.ኤ)

**የጥራት ክትትል፡-**

እንግዳ ዘውዴ(ዶ/ር)

አወቀ ጸጋዬ(ኤም.ኤ)

**የማጣሪያ ንባብ፡-** ኢሳያስ ይልማ(ኤም.ኤ)

**ዲዛይነር፡** ገዳ ሆካ (ኤም.ኤ)



ኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር

ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በትምህርት ሚኒስቴር እና በደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ ትብብር ሲሆን የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም (General Education Quality Improvement Program (GEQIP II) ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት ©2014 ዓ.ም የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሰት ትምህርት ቢሮ ናቸው።

ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

## መውጫ


ምዕራፍ አንድ

ባህላዊ ጋብቻ 1

ምዕራፍ ሁለት

የመስቀል በዓል አከባበር 7

ምዕራፍ ሶስት

ቤተሰብ 14

ምዕራፍ አራት

ውኃ 22

ምዕራፍ አራት

መስህቦቻችን 35

ምዕራፍ ስድስት

ሥነ ቃል 55

ምዕራፍ ሰባት

አርበኝነት 73

ምዕራፍ ስምንት

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች 84

ምዕራፍ ዘጠኝ

ስራና ስኬት 95

ምዕራፍ አስር

አጭር ልቦለድ 104

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ለ5ኛክፍል አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ በተጨማሪም የቃላት፣ የሰዋስው ዕውቀት እንዲያገኙ እንዲሁም የስነ-ጽሑፍ ችሎታን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው አዲሱ አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት አንድ አካል ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለዚህ የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን/መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## መሰረታዊ መርሆዎች

1. ተማሪዎች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርእሰ ጉዳዮች ይማራሉ።
2. ተማሪዎች ስለነዚህ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ።
3. በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ። ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ጽሁፍ ይጽፋሉ።
4. አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል አምስት የቀረቡትን የቃላትና የሰዋስው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ።
5. ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመስርተው የቀረቡ ጽሁፎችን በሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሰሩ ተማሪዎች ይማራሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

፩. የየእለቱን ትምህርት ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ አልያም ከመዛግብት ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ::

፪. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው::

፫. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ::በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ:: ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤

፬. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤

፭. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ::

፮. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ::

፯. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ::

፰. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፤ለምሳሌ:-የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ ተሰድረዋል ወይ? በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ/መካከል/ ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ? ወዘተ.

፱. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ. እንዲጽፉ አበረታቷቸው::

# ምዕራፍ አንድ

# ባህላዊ ጋብቻ

## የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች፡

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ስለ ባህላዊ ጋብቻ ምንነትና አይነት በማዳመጥ ትገልጻላችሁ፡፡
- ስለአንድ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም ስለአካባቢያችሁ ባህል ትናገራላችሁ፡፡
- በቡድን በመወያየት የጋራ ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ፡፡
- ለቃላት/ሐረጋት ቀጥተኛ/መዝገበ ቃላዊ ፍቺና አገባባዊ ፍቺ ተሰጣላችሁ፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት፡

- ጋብቻ
- አስተዳደር
- ባህል
- ዳኝነት
- ሥርዓት

# የመጀመሪያው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አንድ

## የጌዴኦ ብሔረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ስርዓት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ:-

- ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ-ትምህርት በኋላ የጌዴኦ ብሄረሰብ የጋብቻ ስርዓት አይነቶችን እየለያችሁ የራሳችሁን ሀሳብ ትሰነዝራላችሁ/ትሰጣላችሁ።

## ? መልመጃ-፩

፩. የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች:-መምህራችሁ ቀጥለው የሚያነቡላችሁን ምንባብ/ጽሁፍ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን የቅድመ-ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ጋብቻ ምንድን ነው? ጠቀሜታውስ?

ለ የምታዳምጡት ርዕስ ምን ምን ጉዳዮችን/ሀሳቦችን ሊያካትት ይችላል?(ግምታችሁን ግለጹ)።

ሐ. ርዕሱን በተመለከተ የምታዉቋቸውን የሌሎች ብሔረሰቦች የጋብቻ ስርዓቶች (ካሉ) ተናገሩ።

2. ማዳመጣችሁን ቆም ታደርጉና ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ.እስካሁን ያዳመጣችሁት ሥለምን ሥለ ምን ጉዳዮች ነው?

ለ.ቀጥሎ ስለ ጌዴኦ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት ምን ምን ነገሮች(ጉዳዮች) የሚነሱ ይመስላችኋል?

3. የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች (በጽሑፍ መልሱ)

ሀ. በጌዴኦ ብሔረሰብ ያሉት የጋብቻ አይነቶች ስንት ናቸው?

ለ. በብሔረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው የጋብቻ አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. በጌዴኦ ብሔረሰብ ዘንድ ለጋብቻ ሥርዓት ጥሎሽነት የሚቀርቡት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

## ክፍል-ትምህርት ሁለት

### ንግግር

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡-**

- የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም በአካባቢያችሁ ስለሚገኙት ልዩ ልዩ ባህላዊ ስርዓቶች(ክዋኔዎች) ትናገራላችሁ፡፡

### ተግባር-1

1. በአካባቢያችሁ ስለሚገኙ ባህላዊ የዳኝነት(የዕርቅ) ሥርዓቶች የምታውቁትን በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. መጥኖ ያለመውለድ ምን ምን ችግሮችን የሚያስከትል ይመስላችኋል? በጥንድ በጥንድ በመሆን የጋራ ሀሳባችሁን ለሌሎች ግለፁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሶስት

### የኮሬ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር


**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡-**

- የሚቀርብላችሁን ምንባብ በሚገባ በማንበብና ባህል ተኮር(ከባህል ጋር የተያያዙ) ቃላትን/ሐረጋትን በመለየት ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡

### ? መልመጃ-2

ሀ. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ምን ፍቺ ሊኖራቸው ይችላል?

1. እርቀ ሰላም 2. ንግስና 3. መዳኘት 4. ወራሽ



ኮሬዎች የራሳቸው የሆነ ነባር ባህላዊ አስተዳደር አላቸው። ይህ ባህላዊ የአስተዳደር ስልጣን እርከን የስራ ሀላፊነትና የአመራረጥ ስርዓት ያለው ነው። በመዋቅሩ መሰረት የስልጣን እርከኑ ሁሉ ቁንጮ ንጉሱ(ካቴ) ሲሆን ከንጉሱ በታች እንደቅደምተከተላቸው አዋጅቴ፣ዳይነና ኡሹቴ፣ቶራ ማጋ ፍዘና፣ሙራ የሚባሉ የስልጣን አካላት አሉ።

የንግስና ስርዓት በዘር ሀረግ የሚተላለፍ ሲሆን የወራሹ ብቃትና ችሎታ በሽማግሌዎች ይገመገማል። ስልጣኑን የሚረከበው ወራሽ ለጎሳው እስከ 7 ከብቶች እንዲያበረክት ሲጠበቅበት ዋና ዋና ተግባራቱም ሁሉንም ጎሳዎች አስተባብሮ መምራቱ፤ከሱ በታች ላሉ ስልጣን መደልደልና መስጠት ነው። ሴቶች በባህላዊ አስተዳደሩ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ በመሆኑ በአደባባይ የመዳኘት መብት የላቸውም። የንጉሱ ሚስት"ላይሶ" የሚል የማዕረግ ስም ሲሰጣት ንጉሱን በማማከርና በማማለድ በዳኝነት ስርዓት ውስጥ ትሳተፋለች። ባህላዊ ስርዓቱ እንደቀድሞው ጠንካራ አቅም ባይኖረውም አሁንም ብሔረሰቡ እየተጠቀመበት ይገኛል።

በብሔረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች በየደረጃው ባሉ የስልጣን አካላት፣ በሀገር ሽማገሌዎች ይፈታሉ። የጎሳ መሪዎች ተሰብስበው ጉዳዩን ከመረመሩ በኋላ ጥፋተኛው እንዲክስና ይቅርታ እንዲጠይቅ ያደርጋሉ። እውነቱን መካድ የተወገዘ ተግባር በመሆኑ የሚክድ ካለ ይረገማል። በሌላ በኩልም ደግሞ እንደቄስ የሚታዩ የጎሳ ተወላጆች ጣልቃ ይገባሉ። በቀል እንዳይኖር በበግ ደም በግ ከሌለ ደግሞ ውሃ ረጭተው እርቀ ሰላም ይወርዳል።

ግጭቶች ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ከሆነ የሁለቱ ወገን መሪዎች በርቀት ሆነው ሳይተያዩ በአገናኝ ሰው አማካይነት ሽማግሌ በመሰየም ይደራደራሉ።እርቅ ተይዞ በደም ካልታረቁና ፊርስ ካልተበተነ ምግብ አይቀመስም። በመጨረሻም ሁለቱ ወገኖች በአንድ

እቃ እንዲጠጡ ይደረጋል፡፡ በውሳኔ ቅሬታ ያለው ይግባኝ የማለት መብት አለው፡፡ የግጭት መንስኤዎች በጋብቻ፣በድንበር፣እለታዊ ግጭቶችና የበላይነትን በማንጸባረቅ በውስጥ የሚነሱ አለመግባባቶች ሲሆኑ እነዚህ አለመግባባቶች ከላይ በተገለጸው መሰረት በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ የሚፈቱ ናቸው፡፡ ምንጭ:-የደ/ብ/ብ/ህዝቦች ፕሮፋይል፣2008፣64-65፣3ኛ ዕትም

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት/ሐረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ትርጉም ስጡ፡፡

1. እርከኑ
2. ቁንጮ
3. ወራሽ
4. መደልድል
5. ሚና
6. ከመረመሩ
7. የተወገዘ
8. በቀል
9. ይደራደራሉ
10. ባህላዊ መንገድ

# ሁለተኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አራት

### ውይይት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ:**

- በቡድን በመወያየት የጋራ ሀሳብን ለክፍል ጓደኛ ማቅረብ፡፡

### ተግባር-2

በቡድን ሆናችሁ የኮሬ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር የሚለውን ምንባብ መሰረት ላደረጉት ጥያቄዎች የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ (መረጃዎችን በማንበብ) የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹ፡፡

1. ሴቶች በኮሬ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ መሆኑ ለምን ይመስልሃል/ሻል/?
2. ይግባኝ ማለት ምን ማለት ነው?

3. ግጭቶች ለምንና እንዴት ይከሰታሉ? የመፍቻቸው መንገድስ
4. በአካባቢያችሁ አማራጭ(ሌሎች) የግጭት አፈታት ስርዓቶች አሉ? ካሉ በመጥቀስ አብራሯቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አምስት

### መዝገበ ቃላዊ ትርጉም

**መዝገበ ቃላዊ ፍች፡-** ማለት በመዝገበ ቃላት ዝርዝር ውስጥ የሚኖረውን የቃላቱን ቀጥተኛ ትርጉም ይመለከታል፡፡ ምሳሌ፡- በላ=ተመገበ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡**

- ቃላቱን በሚገባ በመመርመር ቀጥተኛ/መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡

### ? መልመጃ-፫

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ስጡ፡፡

1. ሰበሰበ
2. ድርቆሽ
3. መቀመጫ
4. ሐሴት
5. ልጥ
6. ንፉግ
7. ቀና
8. ሰፌ
9. መመርመር
10. ሀብት
11. ዋርካ
12. ላም
13. መንቃት
14. ሽበት
15. ላብ

# ምዕራፍ ሁለት

# የመስቀል በዓል አከባበር

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- ባህል ተኮር ጽሑፎችን መነሻ አድርጋችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- የህዝባዊ በዓላትን አይነትና ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡
- ለአዳዲስና አውዳዊ ቃላት ትርጉም/ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- የባዮ ጋዝ አዘገጃጀት የሚል ጽሑፍን አዳምጣችሁ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- የማስታወሻ አያያዝ ዘዴን ተጠቅማችሁ ንግግር/ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- ባህላዊ
- ህዝባዊ
- አከባበር
- ባዮ ጋዝ

## ሁለተኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### የጉራጌ ብሔረሰብ የመስቀል በዓል አከባበር

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የሚቀርብላችሁን ጽሁፍ በተገቢው ሁኔታ በማንበብ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡

# መልመጃ-4

ሀ. ከዚህ በታች ያሉት ቁልፍ ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ትርጉማቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታችሁን ተናገሩ።

1. አዛውንት 2. መስቀል 3. ደመራ 4. መፈራረቅ

ለ. የቅድመ ንባብ መልመጃ

፩. የጉራጌ ብሔረሰብ በየትኛው ክልልና ዞን የሚገኝ ይመስላችኋል?

፪. የጉራጌ ብሄረሰብ የመስቀል በዓል አከባበርና የሌሎች ብሔሮች የአከባበር ሁኔታ እንዴት ያለ ይመስላችኋል?(ግምታችሁን ተናገሩ)



በብሔረሰቡ የመስቀል፣የገና፣የአረፋ፣የመውሊድና የመሳሰሉት መንፈሳዊ በዓላት ይከበራሉ። ከእነዚህ መካከል የመስቀልና የአረፋ በዓላት ዝግጅት በተለየ መልኩ በድምቀት የሚከበሩ ናቸው። የመስቀል በዓል ዝግጅት ከነሐሴ 12 ቀን ጀምሮ ደመራ በየደጁና በየአካባቢው በማቆም ይጀመራል።

ከዚህ ቀን ጀምሮ ወንዶችም ሴቶችም በየፊናቸው ከበዓሉ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ዝግጅቶችን ማከናወን ይጀምራሉ።ሴቶች እንሰት የመፋቅና ቅቤ የማሰባሰብ ስራ ሲሰሩ ወንዶች ደግሞ እንጨት የመፍለጥና ለከብት መግዣ የሚሆን ገንዘብ የማሰባሰብ ስራ ያከናውናሉ።ዝግጅቱ በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ በዓሉ

በየደረጃው የሚከበረው ከመስከረም 13 ቀን ጀምሮ ሲሆን መስከረም 14ቀን የጎመን ክትፎ ተበልቶ መስከረም 15 ቀን የእርድ ስርዓት ይከናወናል፡፡ከእርድ ቀን ጀምሮ ጥሬ ስጋ በቅቤ/ጫፋየ/፣የጥሬ ስጋ ክትፎ፣የቅቅል ክትፎና ቅቅል ስጋ በቆጮ እየተበላ በዓሉ እስከሚያበቃበት ቀን ድረስ ይቀጥላል፡፡ከመስከረም 13ቀን ጀምሮ በዓሉ እስከሚያበቃበት ቀን ድረስ ያሉት ቀናት የተለያየ ስያሜ አሏቸው፡፡በሰባት ቤት ጉራጌ በዓሉ የሚያቃበት ቀን"አዳብና" ተብሎ ሲጠራ በሶዶ ቤተ ጉራጌ ደግሞ ከመስከረም 16 እስከ ጥቅምት 5ቀን ያለው ጊዜ"አዳብና" ተብሎ ይጠራል፡፡

በእያንዳንዱ አካባቢዎች መስከረም 24 ቀን የበዓሉ ፍጻሜ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቅምት 5 ቀን ይጠናቀቃል፡፡ በአዳብና እለትም የብሔረሰቡ አባላት የቅቅል ስጋ ክትፎ በመመገብ ለቀጣዩ ዓመት መስቀል በሰላም እንዲያደርሳቸው ይመራረቃሉ፡፡የአረፋ በዓልም ከሚከበርበት ጊዜ መለያየትና የእምነቱ ተከታዮች ከሚሰጡት መንፈሳዊ ስያሜ መለያየት በስተቀር በክርስቲያኑ ጉራጌ የሚደረጉት አብዛኞቹ ቅድመና ድህረ የሴትና የወንድ ዝግጅቶች ይከናወናሉ፡፡

በዋዜማው ባህላዊ የጎመን ክትፎ የሚበላ ሲሆን ከእርድ ቀን ጀምሮ ጥሬ ስጋ በቂቤ/ጫፊያ፣የጥሬ ስጋ ክትፎ፣ቅቅል ስጋና የቅቅል ስጋ ክትፎ በቆጮ እየጠበላ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ዕለት ድረስ በየደረጃው በድምቀት ይከበራል፡፡ በብሔረሰቡ ለአዛውንቶች የሚሠጠው ክብርና እንክብካቤ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሽማግሌዎችና በእድሜ የገፉ እናቶች ምርቃት ከፍተኛ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ታሪካዊ ክንዋኔዎችንና የወቅቶችን መፈራረቅ መሰረት ያደረገ የራሳቸው የሆነ የቀን፣የወራት፣የወቅቶችና የዘመን አቆጣጠር አላቸው፡፡

ምንጭ፡- የደ/ብ/ብ/ህዝቦች ፕሮፋይል 2004፣349

## ሐ. ከዚህ በታች ለተቀመጡት ቃላት/ሐረጋት በምንባቡ መሰረት ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. መንፈሳዊ | ረ. በየደረጃው |
| ለ. በድምቀት | ሰ. ስርዓት |
| ሐ. በየፊናቸው | ሸ. እንክብካቤ |
| መ. እንስት | ቀ. ምርቃት |
| ሠ. ሲሰሩ | በ. መፈራረቅ |

# ሶስተኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

### ውይይት/ንግግር

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡**

- በቡድን በመወያየት የጋራ ሀሳብን ማቅረብ፡፡

### ተግባር-3

ቀጣዮቹ ጥያቄዎች ከዚህ ቀደም የቀረበውን ምንባብ መነሻ ያደረጉ ናቸው፤ በቡድን በመወያየት መልስ ፈልጉላቸው፡፡

1. የጉራጌ ብሔረሰብ የመስቀልና የአረፋ በዓላት ከሌሎች በዓላት በተለየ መልኩ በድምቀት የሚከበሩት ለምን ይመስላችኋል?
2. በአካባቢያችሁ የመስቀል በዓል የሚከበር ከሆነ የአከባበሩ ስርዓት እንዴት ያለ ነው?
3. በጉራጌ ብሄረሰብ ልዩ ልዩ አካባቢዎች የበዓላቱ አከባበር ያላቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት አስረዱ፡፡
4. በተገለጹት በዓላት አካባቢና ጊዜ የሚቀርቡ የምግብ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
5. በበዓላቱ አከባበር ምክንያት ማህበረሰቡ የሚያገኛቸው ትሩፋቶች/ጥቅሞች/ ምን ምንድን ናቸው?

## ክፍለ ትምህር ስምንት

### ንግግር

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- በቡድን በመወያየት ስለህዝባዊ በዓላት አከባበር የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቃል ታቀርባላችሁ፡፡


## ተግባር-4

1. በአካባቢያችሁ ስለሚከበሩ ህዝባዊ በዓላት ዓይነትና ጥቅም በጋራ በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
2. ህዝባዊ በዓላቱ መቼና እንዴት ባለ ሁኔታ ይከበራሉ?

## ክፍለ ትምህርር ዘጠኝ:

### ማዳመጥ

## የባዮ ጋዝ አዘገጃጀት




### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የባዮ ጋዝ አዘገጃጀት የሚል ጽሑፍን በማዳመጥ ልዩ ልዩ ተግባራትን መስራት።

## ? መልመጃ-5

ሀ.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ባዮ ጋዝ_______________________ ጋዝ ነው።
   ሀ. ሽታ አልባ      ሐ. የሚያስነጥስ
   ለ. ጪስ አልባ      መ. ሀናለ

2. ባዮ ጋዝ ከሚከተሉት በየትኛው ሊዘጋጅ ይችላል?
   ሀ. ከአሳማ ፍግ　　ሐ. ከከብት ፍግ
   ለ. ከዶሮ ኩስ　　መ. ከሁሉም
3. ፍግን ከውሃ ጋር ቀላቅሎ ላልተወሰነ ጊዜ በጉድጓድ ውስጥ__________ ያስፈልጋል።
   ሀ. መደባለቅ　　ሐ. ማሸግ
   ለ. ማብላላት　　መ. መሰወር
4. ባዮጋዝ ለማዘጋጀት መጠንሰሻ ጉድጓድ ተቆፍሮ ውስጡ__________ ይዘጋጃል።
   ሀ. በሊሾ　　ሐ. በአሸዋ
   ለ. በውሃ　　መ. በእንጨት

**ለ. ቀጥለው የቀረቡት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ"እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ።**

ሀ. ባዮ ጋዝ ለምግብ ማብሰያ፣ለመብራት አገልግሎትና ለአነስተኛ ሀይል ማመንጫ ሞተሮች ይውላል።
ለ. የእንስሳት ፍግ ከውሃ ጋር እኩል መቀላቀል የለበትም።
ሐ. ባዮ ጋዙ ሲመረት የየቀኑን የቤተሰብ ፍጆታ መገመት ያስፈልጋል።

## #የማስታወሻ አያያዝ

- ማስታወሻ መያዝ አንድን ፍሬ ሀሳብ እንዳይዛባ ለማድረግና በቅርስነት ለማስቀመጥ ነው።
- ማስታወሻ መያዝ የሚያስፈልገው አንድ ንግግር ወይም ጽሑፍ ሲነበብ በምናዳምጥበት ጊዜ፣ገለጻ ሲሰጥ ወይም አንድን ጽሑፍ በግል ስናነብ ነው።
- በመሆኑም ወረቀትና ብዕር መያዝ፣ዋና ዋና ሀሳቦችን ወይም መረጃዎችን በቅደም ተከተል መያዝና የተያዘውን ሳያጋንኑ አጠቃሎ መጻፍ ነው።

# አራተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አስር

ውይይት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የማስታወሻ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ ንግግር/ውይይት ማድረግ፡፡

### ተግባር-5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሰዎችን በመጠየቅና የተለያዩ ጽሑፎችን በመመልከት በቡድን ተወያይታችሁ የጋራ ሐሳባችሁን በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

1. ለምግብ ማብሰያነት ከምንጠቀምባቸው ጥንታዊ የሚባሉት ቁሳቁሶች እነማን ናቸው?
2. ለአፈር መሸርሸርና ለድርቅ መከሰት መንስኤ የሆነው ምንድን ነው?
3. በአካባቢያችሁ የሚታወቁት ሌሎች አማራጭ የሀይል ምንጮች ምንድን ናቸው?

# ምዕራፍ ሶስት

# ቤተሰብ

**የምእራፉ አጠቃላይ ዓላማ**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ስለቤተሰብ ምንነት በቃላችሁ ታስረዳላችሁ፡፡
- የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም የእርስ በርስ ልምዳችሁን ትለዋወጣላችሁ፡
- ቤተሰብን በተመለከተ በቀረበው ምልልስ/ጭውውት ላይ በንቃት ትሳተፋላችሁ፡
- ቃላትን በማጥበቅና በማላላት የፍች(ትርጉም) ልዩነትን ታስረዳላችሁ፡፡
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትዘረዝራችሁ፡፡
- የምዕላድን ምንነትና ተግባር ትለያላችሁ፡፡
- ትምህርታዊ መዝሙሮችን አዳምጣችሁ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አስራ አንድ

### ቤተሰብ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የቤተሰብን ምንነት በተመለከተ አዳምጦ መረዳታችሁን ከቀደመ እውቀታችሁ ጋር በማቀናጀት ትገልጻላችሁ፡፡

## ? መልመጃ-6

**ሀ. የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

1. ቤተሰብ ምን ማለት ነው?
2. በየቤታችሁ ስንት የቤተሰብ አባላት አሉ? ስማቸውንና ተግባራቸውን ግለጹ፡፡

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ(በምክንያት አስረዱ)፡፡

1. በጋራ የሚኖሩ የአንድ ቤተሰብ አባላት ችግር ሲያጋጥማቸው ችግራቸውን የሚፈቱት ለየብቻ በመሆን ነው፡፡
2. የእነማቲዎስ ሞግዚት በቤተሰብ አባልነት ልትመዘገብ ይገባል፡፡
3. በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች በመተጋገዝ ስራቸውን ይሰራሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አስራ ሁለት

### ውይይት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- ✅ በጥንድ በጥንድ በመሆን ከቀረቡት የመወያያ ሀሳቦች መካከል አንዱን መርጦ ንግግር ማድረግ መቻል፡፡

## ተግባር-6

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከተወያያችሁባቸው በኋላ ቡድኑ የተስማማበትን ሀሳብ በዝርዝር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. በቤት ውስጥ በአብዛኛው የስራ ጫና ያለበት ማን ነው?ለምን?
2. የቤተሰብ አባላት እንዴት መከባበርና መተጋገዝ እንዳለባቸው ተናገሩ፡፡
3. "ልጆች የጥናትና የጨዋታ መርሀ ግብር አውጥተው መመራት አለባቸው" በሚል ርዕስ ውይይት አድርጉ፡፡
4. እናንተ በቤት ውስጥ የስራ ድርሻችሁ ምንድን ነው? በተራ በተራ አስረዱ፡፡
5. በቤታችሁ ውስጥ ያለውን የስራ የመተጋገዝ ልምድ አስመልክታችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

# አምስተኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አስራ ሶስት

### ጭውውት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- በመጽሐፉ የቀረበውን ተውኔት(የጭውውት ድርሰት) አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን ተከትሎ ጭውውት ማድረግ፡፡

## የጭውውት አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

ጭውውት፡- ሁለት ወይም ከዝያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርስ የሚያካሒዱት የሀሳብ ልውውጥ/ውይይት ነው፡፡ በጭውውት አንዱ ከሌላው የችግሩን መፍቻ ሐሳብ ያገኝበታል፤ልምድ ይጋራበታል፡፡ በጭውውት ጊዜ የእርስ በእርስ መከባበርና መደማመጥ ይታያል፡፡ ጭውውት ቀልዶች የሚታከሉበት ዘና ብሎ የሚካሔድ ነው፡፡ እንዲሁም ጭውውት በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚከናወን ነው፡፡

ጭውውት ተዘጋጅቶ በሚቀርብበት ጊዜ መተኮር ያለባቸው ነጥቦች፡-

- ለስሜት የሚቀርብ ርዕስ መምረጥ
- ርዕሱን በተመለከተ መረዳት
- ተራን ጠብቆ መናገር
- ድምጽን መመጠን
- ፍርሃትና ግዴለሽነትን ማስወገድ
- እራስን ለጭውውቱ ዝግጁ ማድረግና በሚቀርበው ስራ ላይ ብቻ ማተኮር
- አጨራረሱ እንደየሁኔታው ርዕሱ በሚፈቅደው መሰረት ይሁን፡፡ለምሳሌ፡-በሰላምታ መለያየት ወይም ተጣልቶ መለያየት…

## ተግባር-7

ጥንድ ጥንድ በመሆን ከታች የቀረበውን የጭውውት ጽሑፍ በሚገባ በማንበብና በመለማመድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ጭውውት



ኒታ፡- ስማ፣ስማ እባክህ! ጥቅም አይደልልኝም ነው ያልከኝ? ድንቄም እቴ! ስጋ ለባሽ መሆንህን ዘነጋኸው እንዴ?

አሰንቻ፡- ምን ለማለት ፈልገሽ ነው ኒታ?

ኒታ፡- ለማለትማ የፈለኩት፣ሰው መሆንህን ፍፁም ዘንግተህ ራስህን መልዓክ አደረግኸው እኮ ነው የምልህ፤በዚህ ላይ ደግሞ አገር በሙሉ እሱ የጥቅም ሰው ነው የሚልህ!

አሰንቻ፡- ስሚ! ከምን ተነስተው እንደሚሉኝ ታውቂለሽ?

ኒታ፡- ለመሆኑ ምን ሰርተህላቸው ነው?

አሰንቻ፡- ያን በወለድ አገዱ የተያዘ ጎጇቸውን በማስለቀቄ ነዋ!

ኒታ፡- አዬ ጉድ! ለዚያስ ቢሆን ሀምሳ ብር አነሰህና ነው?

አሰንቻ፡- ኧረ በፈጣሪ! ሃምሳ ብር አልሽኝ? እሱማ የልፋቴ ዋጋ ነው።

# ክፍለ ትምህርት አስራ አራት

## የቃላት መጥበቅና መላላት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- ልዩ ልዩ ቃላትን በማጥበቅና በማላላት የሚኖራቸውን የፍቺ ልዩነት ማሳየት መቻል።

## በቃል ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት

1. አንዳንድ የአማርኛ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነገሩ የተለያዩ ትርጉሞች ይሰጣሉ። ምሳሌ:-ቅቤው <u>ለጋ</u> ነው።/ያልበሰለ/
   - -ልጁ ኳሷን <u>ለጋ</u>።/መታ/

   በመጀመሪያው ላይ "ጋ" ፊደል ልል ነው።

   በሁለተኛው ላይ "ጋ" ፊደል ጥብቅ ነው።
2. ቃላት ሆሄያት በስርዓት ተሰባስበው/ተደራጅተው/ የሚፈጥሩት ቅርጽ ነው።
   - ቃላት ከአንድ በላይ ፍቺ ሊኖራቸው ይችላል።
   - ቃላት በመጥበቅና በመላላት ወይም በንባብ ከአንድ በላይ ፍቺ እንዳላቸው ማወቅ የሚቻለው በዓረፍተ-ነገር ውስጥ ሲገቡ ነው።

## ? መልመጃ-7

ሀ. ከዚህ ቀጥሎ በተሰጡት ዓ.ነገሮች ውስጥ ከስራቸው የተሰመረባቸውን ቃላት የያዙትን ፍቺ ሲጠብቁና ሲላሉ በማለት አስቀምጡ።

1. ሀ.የአንደኛ መንፈቀ-ዓመት ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ <u>ገና</u> ነው።

   ለ.<u>የገና</u> በዓል ሲደርስ ልጆች አዳዲስ ልብሶች ይገዛላቸዋል።
2. ሀ.አስተማሪያችን ስም ጠርተው <u>ወጡ</u>።

   ለ.እንጀራና ወጡ ሲያልቅ ክትፎና ቆሎ ይዛ <u>መጣች</u>።
3. ሀ.አባቴ ጫማ እንድገዛበት <u>ሰባ</u> ብር ሰጠኝ።

   ለ.አምና የገዛነው በግ ብዙ ስለተቀለበ <u>ሰባ</u>።

4. ሀ.ለበዓል የሚበሩ ሻማዎች ገዛሁ።

   ለ.በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎች አየሁኝ።

5. ሀ.ከበደ ዋና ሲዋኝ ጎበዝ ነው።

   ለ.እንኳን ትርፍ ዋና ጠፋ።

6. ሀ.አስተማሪያችን"የቤት ስራ ሳትሰሩ እንዳትመጡ" አለች።

   ለ.እኛ ቤትውስጥ ትንሽ ውሻ አለች፤ሰው ሲመጣ ትጮሃለች።

**ለ. ቀጥለው የቀረቡትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ ያላቸውን ፍቺ በመለየት በዓረፍተ-ነገር ውስጥ ተጠቀሙባቸው።**

1. አለ
2. አያት
3. በራ
4. አጠና
5. አዛባ
6. እንስራ
7. ጠላት
8. በኋት
9. ሰፊ
10. ይገባል

## ክፍለ ትምህርት አስራ አምስት

የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የቃላትን እማሬያዊ/ቀጥተኛ/ና ፍካሬያዊ/ኢ-ቀጥተኛ/ ፍች ለይቶ ማስቀመጥ።

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

አንዳንድ የአማርኛ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች አሏቸው። እማሬያዊ ፍች የሚባለው የቃሉ ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍች ነው። ፍካሬያዊ ፍች ደግሞ በተቃራኒ/በአውድ አልያም በዓ.ነገር ውስጥ የሚፈጥረው የፍች ልዩነት ነው።

ምሳሌ፡-"ቤት" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍችው ግድግዳና ጣሪያ ያለው የሰው ልጅ መኖሪያ ማለት ሲሆን፤ፍካሬያዊ ፍችው ደግሞ የአንድ ሰው ጠቅላላ ኑሮ፤ትዳር ወ.ዘ.ተ ማለት ነው።

# ? መልመጃ-8

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሰረት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በማለት ለዩ።

ምሳሌ:- እንጀራ

1. ልጅቷ የጋገረችው እንጀራ ያምራል።(አማሬያዊ ፍች)
2. ልጁ ትምሕርቱን ጨርሶ እንጀራ ወጣለት።(ፍካሬያዊ ፍች)

1. ማር የምታመርት ነፍሳት ንብ ትባላለች።
   ልጅቱ ንብ ነች።
2. እርግብ በሰማይ የምትበር የአዕዋፍ ዝርያ ነች።
   ሰላማዊት እርግብ ናት፡
3. የተለያዩ ነገሮችን አቻችሎ የሚይዝ የአፈር አካል መሬት ይባላል።
   እሱማ ፀባዩ መሬት ነው።
4. ዛፍ ተቆርጦ በመሬት የሚቀረው ክፍል ጉቶ ይሰኛል።
   ብርቱካን ጉቶ ነች።
5. መልኳን የምትለዋውጥ ተሳቢና ተናዳፊ እንሰሳ እስስት ትባላለች።
   ሮዱ ነገረ ስራዋ እንደ እስስት ነው።

## ስድስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አስራ ስድስት

## ምዕላድ(ነጻ ቃልና ቅጥያዎች)

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የምዕላድን ምንነትና አይነት መለየት።

# ? መልመጃ-9

ቀጥለው የተዘረዘሩትን ቃላት በነጻና ጥገኛ(ቅጥያ) ምዕላድ ከነጣጠላችሁ በኋላ፣ በምሳሌው መሰረት በሰንጠረዡ ውስጥ አስፍሩ።

| ተ.ቁ | ቃላት | ዋናው ቃል/ግንድ | ቅጥያ ምዕላዱ |
|---|---|---|---|
| 1. | ልጆች | ልጅ | -ኦች |
| 2. | ሴትነት | ሴት | -ነት |
| 3. | አልበላሁም | በላ | አል-፣-ሁ፣-ም |
| 4. | ተማሪዎች | | |
| 5. | ቤቶች | | |
| 6. | ተራራማ | | |
| 7. | አልመጣም | | |
| 8. | ጠመኔው | | |
| 9. | በጎች | | |
| 10. | አልገባም | | |

## ክፍለ ትምህርት አስራ ሰባት

## ትምህርታዊ መዝሙር

### ንዑስ አላማ

✅ ትምህርታዊ መዝሙሮችን አዳምጣችሁ መልመጃዎችን መስራት።

**ማስታወሻ፡-** አውዳዊ(አገባባዊ) ትርጉም ማለት ከሚቀርብልን ምንባብ ወይም ከምናዳምጠው ትረካ/ግጥም(መነባንብ) የወጡ ቃላትንና ሐረጋትን ወይም ከሚቀርበው ነገር ስሜት ሳንወጣ ፍች የመስጠት ሒደት ነው።

# ? መልመጃ-10

ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን መዝሙር በሚገባ በማዳመጥ ለቀጣዮቹ ቃላት/ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ።

ሀ.ጣዕም ሠ.ትዝታ

ለ.ክረምት ረ.ምንጫችን

ሐ.በመባረቅ ሰ.ሜዳ

መ.ወቅቱ ሸ.ፈነደቅን

# ምዕራፍ አራት

## ውኃ

### የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስዕላዊ መግለጫዎችን ትመለከታላችሁ፤ትናገራላችሁ፡፡
- የውኃ መገኛና ጥቅሙን በማስመልከት ሀሳባችሁን በቃልና በጽሑፍ ታቀርባላችሁ፡፡
- ረጃጅም ከሆኑና ከተቆራረጡ/ካልተቋጩ ሐሳቦች ጋር በመተዋወቅ ሐሳቡን ታሟላላችሁ፡፡
- አቀላጥፎ ማንበብን ትለማመዳላችሁ፡፡
- የቃላትን ተመሳሳይ ትርጉም/ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በዋና ቃል(ግንድ)ና ቅጥያዎች መካከል ያለውን ዝምድናና ልዩነት ታሳያላችሁ/ትገልጻላችሁ፡፡
- ስለ ቃላዊ ግጥም ምንተትና ተግባራት አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቃላዊ ግጥሞችን በሚገባ ታነባላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አስራ ስምንት

### ስዕላዊ መግለጫዎች

#### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- ስዕላዊ መግለጫዎችን መመልከትና መናገር

# ? መልመጃ-0፩:-

ሀ. የሚከተለውን ስእላዊ መግለጫ በሚገባ ከተመለከታችሁ በኋላ ከስር ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡



ስዕል-1





ስዕል-2



ስዕል-3






ስዕል-4

1. በስዕል-1 ላይ ያለው ምንን ይገልጻል?
2. ስዕል-2 ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?
3. በሶስተኛው ስዕል ላይ ምን ተቀምጧል?
4. አራተኛው ስዕል ምንን ያመለክታል?

ለ. ቀጥለው የቀረቡትን ስዕላዊ መግለጫዎች በማወዳደርና በማነጻጸር ገለጻ አድርጉ፡ ፡





ስዕል-1



ስዕል-2

## ሰባተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አስራ ዘጠኝ

### ውኃ ሕይወት ነው፣ውኃ ብርሐንም ነው

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የውኃ መገኛና ጥቅሙን በማስመልከት ሀሳብን በቃልና በጽሑፍ ማቅረብ፡፡

### ? መልመጃ-02

ሀ. አንድ ጽሑፍ መምህራችሁ ከማንበባቸው በፊት በተከታዮቹ ቅድመ-ማዳመጥ ተግባራት ላይ ተነጋገሩ፡፡

1. ውሃን አፍልቶ ወይም አክሞ ካለመጠጣት የሚመጡ በሽታዎች ምን ምንድን ናቸው?
2. ውሃ ከመጠጥ ሌላ ለምን አገልግሎት ይውላል?

ለ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ።

1. ኢትዮጵያ "የውኃ ማማ" የሚል ስያሜ ያገኘችው ከረጅም ዘመናት በፊት ቢሆንም ውሃውን ባለመጠቀሟ ልጆቿ ምን ሆነዋል?
   ሀ.ተርበዋል ለ.ተጠምተዋል ሐ.ለበሽታ ተዳርገዋል መ.ሁሉም መልስ ይሆናሉ
2. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለውኃ የሚዘምሩት እነማን ናቸው?
   ሀ.የበለጸጉ ሐገሮች ለ.አፍሪካውያን ሐ.ያልበለጸጉ ሀገሮች መ.ሁሉም
3. ለኢትዮጵያ ባዳ ሆነው ኖረዋል የተባሉት እነማን ናቸው?
   ሀ.ፏፏቴዎቿ ለ.ወራጅ ውኃዎቿ ሐ.ምንጮቿ መ.ሁሉም
4. ባዳመጣችሁት መሰረት ኤሌክትሪክ ማመንጨት ያልጀመረው የትኛው ግድብ ነው?
   ሀ.ጣና በለስ ለ.ጊቤ አንድና ሁለት ሐ.ተከዜ መ.መልስ የለም
5. ግንባታው እየገሰገሰ ነው የተባለው የትኛው ግድብ ነው?
   ሀ.ህዳሴ ግድብ ለ.ጊቤ ሶስት ግድብ ሐ.ጣና በለስ መ.ተከዜ

## ክፍለ ትምህርት ሀያ

## ረጃጅምና ያልተቋጩ ሀሳቦችን ማሟላት

### ንዑስ አላማ

- ረጃጅምና የተቆራረጡ/ያልተቋጩ ሀሳቦችን ማሟላት።

### ተግባር-8

ቀጥለው በተለያዩ መንገዶች የቀረቡትን ረጃጅምና የተቆራረጡ ሀሳቦችን አሟሉ።

1. እኛ ኢትዮጵያውያን የጀግንነት፣-----፣----ተምሳሌቶች ነን። ሐገራችን በህብረ ብሄራዊነቷ የደመቀች ልዩ ምድር ነች። ህዝቦቿ በአንድነት ሲቆሙ------ሆነው ይታያሉ። ምንም እንኳን ፈተና ቢጋረጥባትም በፈጣሪዋ ድጋፍና በልጆቿ ፅናት፣ብርታት...ለዘላለም ትኖራለች።
2. እንስሳት በሁለት አበይት መደቦች ይከፈላሉ። እነሱም የቤትና የዱር እንስሳት በመባል። የቤት እንስሳቱ ላም፣በግ፣-----፣----፣----፣---፣---፣

ሲሆኑ፣የዱር እንስሳቱ ደግሞ አንበሳ፣ጅብ፣------፣----፣----፣----፣---፣----፣----ናቸው፡፡

3. ሙዚቃ በመሳሪያዎች ተቀነባብሮ የሚቀርብ ልዩ የስሜት መግለጫ ነው፡፡ በመሆኑም ባህላዊና ዘመናዊ መሳሪያዎችን ይጠቀማል፡፡ ባህላዊ መሳሪያዎቹ ክራር፣ከበሮ፣-----፣-----፣-----፣...ሲሆኑ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎቹ ደግሞ ኪቦርድ፣------፣------፣-------፣...ናቸው፡፡
4. ኮቪድ19 እ.አ.አ በ2019ና በእኛ በ2012ዓ.ም የተከሰተ አደገኛና ተላላፊ በሽታ ነው፡፡በሽታው በትንፋሽ፣--------፣-------፣...ይተላለፋል፡፡ቅድመ መከላከያው ደግሞ የአፍ መሸፈኛ (ጭንብል) ማድረግ፣--------------፣-----------፣------------፣.....ነው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሀያ አንድ

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የቀረበውን ምንባብ በአቀላጥፎ ማንበብ መመሪያዎች መሰረት የንባብ ክሂል ደረጃን ማየት፡፡

### ማስታወሻ

**አቀላጥፎ ማንበብ** ፡-ቃሉ እንደሚያመለክተው በንባብ ወቅት የሚኖረውን የጊዜ አጠቃቀም ያመለክታል፡፡ እያንዳንዱን ፊደል እየቆጠርን የማንበብ ልምዳችንን ለማሻሻል ይጠቅማል፡፡ የአነባበብ ፍጥነት የሚለካው በአንድ ደቂቃ ምን ያህል ቃላት አንብበን መልዕክቱን መረዳት እንደምንችል በማስላት ነው፡፡ በአንድ ደቂቃ አስር ወይም አስራ አምስት ቃላት ብቻ ካነበባችሁ አዝጋሚ አንባቢዎች ናችሁ ማለት ነው፡፡ በአንድ ደቂቃ መቶ ቃላት ማንበብና መረዳት ብትችሉ ፈጣን አንባቢዎች ናችሁ ማለት ይቻላል፡፡ አዘውትሮ በማንበብ የንባብ ፍጥነት ይሻሻላል፤ለፍጥነት ንባብ የሚከተሉትን መመሪያዎች ተከተሉ፡-

- የምታነቡትን ፅሑፍ ለአይናችሁ በሚያመች ሁኔታ ያዙ፤
- በጣት የመጠቆም ፀባይ ካላችሁ አስወግዱ፤
- ከንፈር በመግጠም በዓይን እንቅስቃሴ በማየት/የተሳናችሁ ከሆነ በመዳሰስ/ ብቻ አንብቡ እንጂ ድምፅ አታሰሙ፡፡

- ማንበብ ስትጀምሩ ሰዓት ይዛችሁ፣ስታቆሙ ደግማችሁ ሰዓት በማየት በአንድ ደቂቃ ምን ያህል ቃላት እንዳነበባችሁ ቁጠሩ፡፡ክንውኑን በመደጋገም ያሳያችሁትን መሻሻል ተገንዘቡ፡፡
- ከአቀላጥፎ ንባብ በኋላ የፅሑፉን መልዕክት ስለመረዳታችሁ ራሳችሁን ጠይቁ ወይም ተረድቻለሁ የምትሉትን ለጓደኞቻችሁ በመናገር ተወያዩበት፡ ፡

## የእናት ጡት ወተት አስፈላጊነት

የእናት ጡት ወተት በጣም ጣፋጭ የሆነ፣በህጻን አንጀት በቀላሉ የሚፈጭና ለሕፃናት እድገት የሚያስፈልጉትን አልሚ ምግቦች አሟልቶ የያዘ ምግብ ነው፡፡ በመሆኑም ህጻናትን ከበሽታ ለመፈወስም ሆነ ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡

የጡት ወተት አዲስ ለተወለዱ ህጻናት ከሁሉ የተሸለ ምግብ ስለሆነ፤ሕጻናት ምንም ዓይነት ተጨማሪ ምግብ አያስፈላጋቸውም፡፡ የህክምና ጥናቶች እንዳረጋገጡት አንድ ህጻን ከተወለደ ከአራት እስከ ስድስት ወራት ድረስ ተጨማሪ ምግብ አያስፈልገውም፡ ፡በውስጡ ያሉ ፕሮቲኖች፣ቅባቶችና ቫይታሚኖች የተሟሉ በመሆናቸው የህጻኑን እድገት ጥንካሬ ያፋጥናሉ፡፡ የጡት ወተትን የሚተኩ ምግቦችን ለማዘጋጀት ብዙ ጥረት ቢደረግም እስካሁን የሚወዳደረው አልተገኘም፡፡

የእናት ጡት ወተት ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ሀይሎችን ስለያዘ፣ህጻናት በቀላሉ በበሽታ እንዳይጠቁ ይረዳቸዋል፡፡ ጡት የሚጠቡ ህጻናት የተለያዩ በሽታዎች ቢይዟቸው እንኳን ጡት የማይጠቡትን ያህል አይጠናባቸውም፡፡ በሽታ ለመቋቋም የሚያስችል ሐይል ስለሚያገኙ ቶሎ ይሻላቸዋል፡፡ በተጨማሪ ጡት የጠቡ ህጻናት በጥርስ፣በካንሰር፣በስኳርና በመሳሰሉት በሽታዎች የመያዝ ዕድላቸው አነስተኛ ነው፡ ፡ በአንጻሩ ጡት ያልጠቡ ሕፃናት ለተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡና በተመጣጠነ ምግብ እጦት ተጠቂ ናቸው፡፡



ጡት ማጥባት ለሕጻናት ብቻ ሳይሆን ለእናቲቱም ይጠቅማታል።ጡቷ የበለጠ ወተት እንዲያመነጭ ይረዳታል። ጡት የምታጠባ እናት ቀጣዩን የእርግዝና ጊዜ ልታረግዝም ትችላለች። የእርግዝና ወቅቶች ማራዘም ደግሞ እናቶችና ህጻናት ይበልጥ ጤናማ እንዲሆኑ ይረዳል። ከዚህም በተጨማሪ ጡት የሚያጠቡ እናቶች በማህጸንና በጡት ካንሰር የመያዝ ዕድላቸው እጅግ አነስተኛ ነው።

ጡት ማጥባት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ውስጥ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት በእናትና በልጁ መካከል የሚኖረው ትስስር ነው። ህጻኑ ከእናቱ ጋር ያለቃላት ግንኙነት ለማድረግ ገላ ለገላ በመነካካት ሙቀት ለማግኘት ይረዳዋል። ይህም ለልጁ ማህበራዊና ስነልቦናዊ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። በመሆኑም እናቶች ልጆቻቸውን በሚገባ እንዲያጠቡ ይመከራል።

ምንጭ:-አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣6ኛክፍል፣1998፣102-103(መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት)

## ? መልመጃ-0፫

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው።ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ።

1. የጡት ወተት አዲስ ለተወለዱ ህጻናት ከሁሉ የተሻለ ምግብ ነው።
2. ጡት ማጥባት ህጻናትን ከሞት ያድናል።
3. ጡት ማጥባት ለህጻኑ ብቻ እንጂ ለእናቲቱ ምንም ጥቅም አይሰጥም።

ለ. ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እንደአጠያየቃቸው በጽሑፍ ምላሽ ስጡ።

1. ለሕፃናት የእናት ጡት ወተት ከሁሉ የበለጠ ተፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
2. ሕፃናት ጡጦ እንዳይጠቡ የሚመከረው ለምንድን ነው?
3. የእናት ጡት ወተት የጠቡና ያልጠቡ ህጻናት ምን ልዩነት ሊታይባቸው ይችላል?

# ስምንተኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሀያ ሁለት

### የቃላት ተዛማጅ(ተመሳሳይ) ትርጉም

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የልዩልዩ ቃላትን ተመሳሳይ ትርጉም/ፍች ለይቶ ማስቀመጥ።

## ? መልመጃ-04

ሀ. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተመሳሳያቸውን ፈልጉላቸው።

-ምሳሌ፡-ረዳት፡-አጋዥ

-እኩያ፡-አቻ

| | | |
|---|---|---|
| 1. መንስኤ | 4.ቀረፈ | 7.ዱካ |
| 2. ሰነዘረ | 5.ፋና | |
| 3. መዓት | 6.ተመገበ | |

ለ. ከዚህ በታች በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ክፍል በፍች ተመሳሳይ የሆነውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ሥርዓት | ሀ.መደነቅ |
| 2. ትህትና | ለ.አክብሮት |
| 3. መገረም | ሐ.ደንብ |
| 4. ተግዳሮት | መ.ችግር |
| 5. ትዕግስት | ሠ.መለካት |
| 6. መድፈር | ረ.አለመፍራት |
| 7. መመጠን | ሰ.መቻል |
| | ሸ.ማወላወል |

## ክፍለ ትምህርት ሀያ-ሶስት

### ግንድና ቅጥያዎች

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- በዋና ቃል(ግንድ)ና ቅጥያዎች መካከል ያለውን ዝምድናና ልዩነት ማሳየት/መግለጽ፡፡

## ? መልመጃ-05

ሀ. በሚከተሉት ዋና ቃላት ላይ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎች እንዳስፈላጊነታቸው በመጨመር ሌሎች ቃላትን መስርቱ፡፡

| ተ.ቁ | ግንድ/ዋና ቃል | መነሻ ቅጥያ | መድረሻ ቅጥያ | መነሻና መድረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ዘራ | ተዘራ | ዘራው | የተዘራው |
| 2. | ሰጠ | | | |
| 3. | ፈለገ | | | |
| 4. | ወሰደ | | | |
| 5. | ገለፀ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6. | በላ | | | |
| 7. | ገለበጠ | | | |
| 8. | ፈራ | | | |
| 9. | ቀበረ | | | |
| 10. | ደበቀ | | | |
| 11. | ወሰነ | | | |

ለ. በሚከተሉት ቃሎች ውስጥ የትኞቹ መነሻ ቅጥያዎች፣የትኞቹ ግንድ፣የትኞቹ ደግሞ መድረሻ ቅጥያዎች እንደሆኑ ተንትናችሁ አመልክቱ፡፡የመጀመሪያው ለምሳሌ ያህል ተሰርቶላችኋል፡፡ቃሉ መነሻ ወይም መድረሻ ቅጥያ ከሌለው ሰረዝ አድርጋችሁ እለፉት፡፡

| ተ.ቁ | ቃሉ | መነሻ ቅጥያው | ግንድ | መድረሻ ቅጥያው |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ከልጆች | ከ- | ልጅ | -ኦች |
| 2. | ለችግሩ | | | |
| 3. | ፍላጎቶች | | | |
| 4. | የቤተሰብ | | | |
| 5. | የልጆችን | | | |
| 6. | በየሜዳው | | | |
| 7. | ከልጆቹ | | | |
| 8. | ጤናቸውን | | | |

## ክፍለ ትምህርት ሀያ አራት

### ቃላዊ ግጥሞች

#### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- በተሰጠው ቃላዊ ግጥም መሰረት የአዳምጦ መረዳት መልመጃዎችን መስራት፡፡

# መልመጃ-06

## ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት በቡድን በመነጋገር በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. "ቃላዊ ግጥሞች ባለቤታቸው ህዝብ ነው" የተባለው ለምን ይመስላችኋል?
2. ሰዎች ቃላዊ ግጥሞችን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፉበት ምክንያት ምንድን ነው?

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት መሰረት ተስማሚውን አማራጭ በመለየት መልሱ።

1. በቃላዊ ግጥሞች ውስጥ <u>የማይካተተው</u> የትኛው ነው?
   ሀ.ፉከራ ለ.ተረት ሐ.ቀረርቶ መ.ሙሾ
2. ቃላዊ ግጥሞችን በሚመለከት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. በመልካም ስነ-ምግባር ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋሉ።
   ለ. ፀሐፊያቸው/ደራሲያቸው ይታወቃል።
   ሐ. አንባቢን ወይም አድማጩን አያዝናኑም።
   መ. ታሪክን ለማጥናት እንደመረጃ ምንጭ አያገለግሉም።
3. የቃላዊ ግጥሞች ባለቤት የማይታወቀው ለምንድን ነው?
   ሀ. ደራሲ ስላላቸው፤
   ለ. የፈጠራቸውን ደራሲ በትክክል ስለማይታወቅ/የህዝብ ሐብት በመሆናቸው
   ሐ. ሰዎች በየግላቸው ስለሚፈጥሯቸው፤
   መ. የበርካታ ሰዎች አሻራ ስለማያርፍባቸው፤

ሐ. በ“ሀ” ክፍል ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ባዳመጣችሁት መሰረት ከ“ለ” ክፍል ተመሳሳያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ይንፀባረቃል | ሀ. እርካታን ይፈጥራሉ |
| 2. ቁጥብ | ለ. ባህል፣ወግ |
| 3. ያዝናናሉ | ሐ. ተመርጦ |
| 4. መልካም ስነ ምግባር | መ. ጥሩ ባህሪ |
| 5. ልማድ | ሠ. ይታያል |
| | ረ. የተመጠነ |

# ዘጠነኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሀያ አምስት

ባህላዊ ግጥም(ቃላዊ ግጥም)

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የግጥም አነባብ ስልቶችን ተከትሎ አጫጭር ባህላዊ(ቃላዊ) ግጥሞችን በሚገባ ማቅረብ መቻል።

### ማስታወሻ

- ግጥም የሚመሰረተው በስንኝ ነው። ስንኝ ደግሞ አንድ የግጥም መስመር ነው።
- አንድን ግጥም አቀላጥፎ ለማንበብ የሚረዱ መሪያዎች፡-
  - በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆምታ ማድረግ፣
  - ግጥሙን በተገቢው ዜማና ቃና(የግጥሙ ስሜት) ማንበብ፣
  - የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ከሬዲዮ፣ከቴልቪዥን፣ከሥነ-ጽሑፋዊ መድረኮች ወ.ዘ.ተ ማዳመጥ፣
  - ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሳ፣ ... መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደግጥሙ ዓይነት እያቀያየሩ ለማንበብ መሞከር

# መልመጃ-07

ሀ. መምህራችሁ ባሳዩዋችሁ የግጥም የአነባበብ ስልት መሰረት ቀጣዮቹን ልዩ ልዩ አጫጭር ግጥሞች ዜማቸውንና ቃናቸውን በመጠበቅ በየተራ አንብቡ፡፡

1. የሰርግ ቃላዊ ግጥም

ሀ.የሙሽሪት እናት ውጪ ተከሰሻል፣
ይህቺን መሳይ ቆንጆ ማን ውለጅ ብሎሻል፡፡

ለ.እንዳላይሽ እንዳላይሽ፣
ወርቁን ጋረዱት ሚዜዎችሽ፡፡

2. የእርሻ ቃላዊ ግጥም

ሀ.ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ፤
ራብ ክፉ ነው ይገላል አንቆ፡፡

ለ.ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ፣
አይላትም ሚስቱን ቆጥበሽ እደሪ፡፡

3. የሙገሳ ቃላዊ ግጥም

ሀ.የእኔ ሴት ወይዘሮ የኔ ስመ መልካም፣
በእጇ ስራን እንጂ በአፏ ሰው አትነካም፡፡

ለ.የኔማ እመቤት የፈተለችው፣
የሸረሪት ድር አስመሰለችው፡፡

4. የሀዘን ግጥም/ሙሾ/

ሀ.አንተ አለኸኝ ብዬ ስመካ ስመካ፣
አወይ የሰው ነገር ሞተህ ነወይ ለካ፡፡

ለ.ሲሰራው ዋለና ሲያንፀው ሲያንፀው፣
እንደመፋቅያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው፡፡

ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት/ሐረጋት በትዕዛዝ-፩ ላይ ከቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች የተውጣጡ ናቸው፡፡ እንደአገባባቸውም አውዳዊ ፍች ፈልጉላቸው፡፡

1. ጋረዱት
2. እርፍን
3. እዳሪ
4. ሲያንፀው
5. ስመ መልካም
6. ድር

# ምዕራፍ አራት

# መስህቦቻችን

## የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በአካባቢያችሁ እንዲሁም በሀገራችሁ ስላሉ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ መስህቦች ልዩ ልዩ መረጃዎችን ታነባላችሁ፤
- የተለያዩ ክርክሮችንና ምልልሶችን ታዳምጣላችሁ፤
- የስርዓተ-ነጥቦችን ምንነት፣ዓይነትና አገልግሎት ትለያላችሁ፤
- ውይይት ታካሂዳላችሁ፤
- የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የቃል ክፍሎችን አይነትና አጠቃቀም ትለያላችሁ፡፡፤
- ጥምር ቃሎችን ትመሰርታላችሁ፤
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ታዛምዳላችሁ፤
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- ቀለል ያሉ ሥነ-ጽሑፎችን(ተረትና ምሳሌን)ታነባላችሁ፡፡

# ዘጠነኛው ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሀያስድስት

## መስህቦቻችን

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- በአካባቢያችን እንዲሁም በሀገራችን ስላሉ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ መስህቦች ልዩ ልዩ መረጃዎችን ማንበብ።



## ? መልመጃ-08

**ሀ. የቅድመ ማንበብ ተግባራት፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን በቃላችሁ ግለፁ።

1. መስህብ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. "መስህቦቻችን" ከሚለው ምንባብ በላይ ከቀረቡት ስዕሎች ምን ተረዳችሁ? ምክንያት መስጠት ትችላላችሁ?

ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚችሉ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ መስህቦች ባለፀጋ ናት። ከተፈጥሯዊ መስህቦቿ መካከል ተራራዎች ፣ፏፏቴዎች ፣ሐይቆች ፣ብርቅዬ እንስት፣የአዕዋፍ ዝርያዎችና ዕፅዋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመሬት በታች ከአንድ ወጥ አለት ተፈልፍለው የተሠሩ ዕፁብ ድንቅ የላልይበላ ውቅር ኣብያተ ክርስቲያናትን መጥቀስ ይቻላል።እዲሁም የ17ኛውና የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የታሪክ ውጤቶች የሆኑት የጎንደር አብያተ መንግሥታት ሰው ሠራሽ መስህቦች ናቸው በተጨማሪም የነገሥታትን ታሪክ የሚያሣዩ ሀውልቶች፣ በተለያዩ ዘመናት የተሠሩ ቤተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትናመስጊዶች ይጠቀሳሉ።

ኢትዮጵያ ከባህር ወለል በላይ 4620 ሜትር ከፍታ ካለው የራስ ዳሽን ተራራ ጀምሮ፣ከባህር ወለል በታች 116 ሜትር ዝቅታ እስካለው የዳሎል ረባዳ ቦታድረስ የተለያዩ መልክዓ-ምድራዊ ገጽታዎች አሏት።ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ፏፏቴዎች የሀገሪቱ ድንቅ መለያዎች ናቸው።ከነዚህም መካከል የጢስ አባይ፣ የአጆራ፣የትስኪ፣የፏንግና የዶንዶር ፏፏቴዎች ይጠቀሳሉ።ሁሉም የጎብኚዎችን ቀልብ የመሳብ ኃይል አላቸው።

የጢስ አባይ ፏፏቴ ከባህር ዳር ከተማ በስተምሥራቅ ይገኛል።ፏፏቴው ወደ ገደል ሲወረወር እጅግ አስገራሚና አስደሳች ክስተት ይፈጥራል። እየተጥመለመለ ወደገደሉ ከሚወርደው ውኃ የሚፈጠረ የውኃ ፍንጥቅጣቂ ጢስ የተባዘተ ጥጥ ይመስላል። የፏፏቴው ነጎድጓድ-ድምፅ፣ የአካባቢው ልምላሜና የውኃው ጢስ የሚፈጥረው ቀስተደመና ለመንፈስ ደስታ ይሰጣል።

በሌላ በኩል በደቡብ-ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የአጆራ መንትያ ፏፏቴዎች የጎብኚዎችን ቀልብ ከሚስቡት መስህቦች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በሁለቱ ፏፏቴዎች መካከል ያለው ርቀት በቀጥታ መስመር ሲለካ 650 ሜትር እንደሚሆን ይገመታል። ከፏፏቴዎቹ የሚፈጠረው ድምጽና ሻሽ መሰል ነጭ ጢስ ከመልክዓ ምድራዊ ልምላሜ ጋር ተደምሮ ለአካባቢው ልዩ ውበት ሰጥተውታል። እነዚህ ወንዞች ከፏፏቴው አለፍ ብለው ውህደት ይፈጥሩና አበይት ከሚባሉት የኢትዮጵያ ወንዞች መካከል አንዱወደ ሆነው የኦሞ ወንዝ ይቀላቀላሉ።

ኢትዮጵያ ከራስ ዳሽን ከፍታ እስከ ዳሎል ዝቅታ ድረስ ያሏት የተፈጥሮ ገጽታዎች ውበት ሰጥተዋታል። ኢትዮጵያ የጎብኚዎችን ቀልብ የሚስቡ በርካታ

ፏፏቴዎች ያላት ሀገር ናት፡፡

በኢትዮጵያ ብዙ ብሔራዊ ፓርኮችና መስህቦች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አዋሽ፣አብያታ፣ ሻላ፣የባሌ ተራሮች፣የሰሜን ተራሮች፣ነጭሣር፣ማጎ፣ ኦሞ፣ ጋምቤላ፣አርባ ምንጭ የአዞ እርባታ ጣቢያ፣ባቢሌ የዝሆን መጠለያ፣ ሰንቀሌ የቆርኪዎች መጠለያና ማዜ ብሔራዊ ፓርኮች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ መስህቦች ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣የአዕዋፍ ዝርያዎችና የሌሎችም የተፈጥሮ ብዝኃ ሕይወት መገኛዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ኢትየጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠ ራ ሽ መስህቦች ባለቤት በመሆኗ በቱሪዝም ሀብቷ ተጠቃሚ ናት፡፡ ስለዚህ እነዚህን ሀብቶች ልንጠብቃቸውና ልንከባከባቸው ይገባል፡፡

(አ.ብ.ክ.መ ባቱ.ማ.ቢሮ፡፡የአማራ ክልል የቱሪዝም መስህብ ሀብቶች፡፡ 1991 ዓ.ም.፡፡እና ከድረ ገጽ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቡድን በመወያየት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. መስህቦች በስንት ይመደባሉ? ጥቀሷቸው፡፡
2. ኢትዮጵያ ካሏት መስህቦች ምን ጥቅም ታገኛለች?
3. የሀገራችንን ጎብኚዎች የሚያስተናግዱ ተፈጥሯዊ መስህቦችን ጥቀሱ?
4. የጢስ አባይ ፏፏቴ መገኛው የት ነው?

ሐ. ለሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ሁለንተናዊ ለ. ሲወረወር ሐ. ይቀላቀላሉ መ.ወለል ሠ.ብርቅዬ
ረ. መስህቦች ሰ. የበርካታ ሸ.ባለፀጋ ቀ.ክፍለ ዘመን

# ክፍለ ትምህርት ሀያ ሰባት

ክርክር

## የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የክርክርን አዘገጃጀትና አቀራረብ ዘዴን ተከትሎ የተዋጣለት ክርክር ማካሔድ፡ ፡

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር፡- ሁለትና ከዝያ በላይ የሖኑ ሰዎች/ቡድኖች በአንድ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ጎራ/ቡድን/ በመያዝ ለማሸነፍና ለመሸነፍ የሚያደርጉት የሀሳብ ፍልሚያና የመረጃ መለዋወጫ ስልት ነው።

በክርክር ጊዜ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ስጡ፡-

- በቂ ዝግጅት ማድረግ፤
- ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ሐሳቦችን ማቅረብ፤
- የሚቀርቡ ሐሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ተራን ጠብቆ መናገር፤
- የሌላን ሰው ሀሳብ አለማንቋሸሽ፤
- ለተቃዋሚ ሀሳብ ተገቢ መልስ መስጠት፤

በክርክሩ ላይ የሚሳተፉት አካላት የስራ ድርሻ፡-

## የሊቀመንበር ተግባር

- ለታዳሚዎች ሰላምታ በማቅረብ መድረኩን ይከፍታል፤
- የመከራከሪያ ሀሳቦችን ለተሳታፊዎች ያስተዋውቃል፤
- ዳኞቹንና  የሁለቱን ጎራ ተከራካሪዎች ያስተዋውቃል፤
- ታዳሚዎች ክርክሩን በጥሞና እንዲከታተሉ በአክብሮት ይጠይቃል፤
- መድረኩን በበላይነት ይመራል፤ይቆጣጠራል፤

- የክርክሩን ውጤት ለታዳሚዎች ያሳውቃል፤
- የክርክሩን(የመድረኩን) ታዳሚዎች፣ዳኞች፣ተከራካሪዎች አመስግኖ ማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ይቋጫል፡፡

## የዳኞች ተግባር

- በክርክር ስርዓትና አቀራረብ መሰረት በተዘጋጀው የነጥብ መስጫ ቅፅ(ፎርም) ላይ ለእያንዳንዱ ተከራካሪ በየግላቸው ነጥብ ይሰጣሉ፤
- እያንዳንዱ ተከራካሪ በቅፁ ላይ በተቀመጠው መመዘኛ መስፈርት ተመልክተው ሚዛናዊ የሆነ ዳኝነት(ነጥብ) ይሠጣሉ፤
- የእያንዳንዱን ተከራካሪ እንቅስቃሴ በአትኩሮት ይከታተላሉ፤
- ከሊቀመንበሩ ጋር ኅብረት በመፍጠር የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፤
- በየግላቸው የያዙትን ነጥብ አጠናቅረው ለሊቀመንበሩ ያቀርባሉ፡፡

## የተከራካሪዎች ተግባር

- ስለሚከራከሩበት ርዕስ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን ከሚያውቅ ሰው ወይም ከመጽሐፍ ማሰባሰብ አለባቸው፤
- የሚያገኙትን ሀሳብ በቁራጭ ወረቀት አቀናብረው ማስታወሻ መያዝ አለባቸው፤
- ክርክሩን ሲጀምሩ መምህራንን፣ዳኞችን፣ሊቀመንበርን በአክብሮት ማንሳት አለባቸው፤
- የተቃራኒውን ቡድን ሰምቶ የመቃወሚያ ሀሳብ ማቅረብ ያስፈልጋል፤
- የተፈቀደውን ሰዓት ማክበር ያስፈልጋል፡፡

### ተግባር-9

በቡድን በቡድን በመደራጀት የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያን ተከትላችሁ በመረጣችሁት የመከራከሪያ ርዕስ ዙሪያ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሰረት ጎራ/ወገን/ በመያዝ ተከራከሩ፡፡

1. የቤተሰብ ብዛትን መመጠን ይጠቅማል/ይጎዳል?
2. ከትምህርትና ከንግድ የቱ ይሻላል?
3. ከከተማና ከገጠር ኑሮ የቱ ይሻላል?

# ክፍለ ትምህርት ሀያ ስምንት

## ሥርዓተ ነጥቦች

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የስርዓተ ነጥቦችን አይነትና አገልግሎት በልዩ ልዩ መንገዶች መጠቀም፡፡

## ሥርዓተ ነጥቦች

ስርዓተ ነጥቦች የንግግር ድምጽ ወክለው ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡ሐሳባችንንም በፅሁፍ በምንገልፅበት ጊዜ የምንጠቀምባቸው ምልክቶች ናቸው፡፡ የተዘረዘሩ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ዓ.ነገሮችን ለመለየት፤ዓ.ነገርን ለመቋጨት፤አድናቆትን ለመግለጽ፤የሰው ሀሳብ መሆኑን ለመጠቆም፤ወዘተ ከፍተኛ አገልግሎት አላቸው፡፡

በጽሑፍ ጊዜ ከምንጠቀምባቸው በርካታ ሥርዓተ ነጥቦች መካከል፡-

### የጥያቄ ምልክት(?)

- መልስ ለሚፈልጉ ጉዳዮች/ሀሳቦች/ ማመላከቻነት ይጠቅማል፡፡

  ምሳሌ፡- -ስምህ ማነው?

  -ትምህርት መቼ ይጀመራል?

### 1. ነጠላ ሰረዝ(፣/፥)

- የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለያየት ያገለግላል

  ምሳሌ፡- አበበ፣ከበደ፣ለማና አየለ ጓደኞሞች ናቸው፡፡

- ተከታታይ ሐረጎችን ለመለያየት ይጠቅማል፡፡

  ምሳሌ፡- ፊቴን ታጥቤ፣ቁርሴን በልቼ፣ደብተሬን ይዤ፣ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩ፡፡

- ምዕራፍን ከቁጥር ለመለያየት ይውላል፡፡ ምሳሌ፡-ዮሐ.4፥5

## የጥቅስ ምልክት(“ ”)

- በጽሑፍ ውስጥ የሌላ ሰው ንግግርን የምንለይበት ምልክት ነው፡፡
  ምሳሌ፡- ርዕሰ መምህሩ “መማር ያስከብራል፤ስንፍናንም ያስቀራል!” ሲሉ መከሩን፡፡

## ትዕምርተ አንክሮ/ቃለ-አጋኖ(!)

- በጽሑፍ ውስጥ ልዩ ልዩ ስሜቶችን መግለጫ ነው፡፡ ደስታን፣አድናቆትን፣ማበረታታትን፣ማዘዝን...ይገለጽበታል፡፡
  ምሳሌ፡-1.ጎሽ የኔ ልጅ! ጥሩ አደረግክ፡፡
  2.ትምህርትህን በሚገባ ተማር!
  3.ለውጤት በጋራ እንትጋ!

## ? መልመጃ-09

ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥቦች አስገቡ፡፡

1. የጠረጠረ እሾህ አጠረ ያልጠረጠረ ተመነጠረ አለ ከበደ
2. ወደ አርባ ምንጭ የምትመለሰው መቼ ነው
3. ጎጂ ነፍሳት የሚባሉት ዝንብ የወባ ትንኝ አንበጣ ወዘተ ናቸው
4. የአካባቢና የግል ንጽህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው
5. ሁላችንም ለሀገራችን ዘብ እንቁም ወታደርም እንሁን

ለ. የሚከተሉትን ሥርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ እናንተም ምሳሌውን በመመልከት መልመጃውን ስሩ፡፡

| ተ.ቁ | የስርዓተ ነጥቡ ስም | ምልክቱ | ምሳሌ(በዓ.ነገር ሲገባ) |
|---|---|---|---|
| 1. | ነጠላ ሰረዝ | ፣ | ችግኝ ለማፍላትዶማ፣አካፋ፣ መኮትኮቻ ወዘተ ያስፈልጋል፡፡ |
| 2. | የጥያቄ ምልክት | ______ | ______________________ |

3. ቃለ አጋኖ_____________ ______________________________

4. ትዕምርተ ጥቅስ_____ ______________________________

# አስረኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሀያ ዘጠኝ፡-

### ውይይት





### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡

- የውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ ስልትን ተከትሎ በጋራ መነጋገርና የመፍትሔ ሀሳቦችን ማመንጨት፤የጋራ መግባባት ላይም መድረስ፡፡

### ተግባር-10

ሁለትና ከዚያ በላይ በመሆን ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ የደረሳችሁበትን ነጥብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

### የመወያያ ነጥቦች

1. የግልና የአካባቢ ንፅሕናን እንዴት መጠበቅ ይቻላል?
2. መስህቦቻችንን ከጉዳት መታደግና ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገር የሚቻለው እንዴት ነው?
3. በረሃማነት እንዳይከሰት ምን ማድረግ አለብን?
4. በትምህርት ላይ ያሉ ችግሮች ምን ምንድን ናቸው? መፍትሄውስ?

# ክፍለ ትምህርት ሰላሳ

## የቃል ክፍሎች

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የቀደመ እውቀትን መሰረት በማድረግ ዋና ዋና የቃል ክፍሎችን አይነትና አጠቃቀም መለየት፡፡

## የቃል ክፍሎች

የቃላት ምንነት :-ቃል ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሹ ቃል ማለት ትርጉም (ፍች) ያለው፣ ከያዘው የቋንቋ ቅርጽ በታች ሊሸነሸን የሚችል፣ በውስጡ በርካታ ቅጥያ ምዕላዶችን ሊያስቀጥል የሚችልና ከቃል ክፍሎች ባንዱ የሚመደብ የቋንቋ መዋቅራዊ ደረጃ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አምስት ዋና ዋና የቃል ክፍሎችን እናገኛለን፡፡እነሱም:- ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ተውሳከ ግስና መስተዋድድ ናቸው፡፡ ስም የምንለው የነገሮች፣ የቦታዎች፣ የሰዎች...መጠሪያ/ስያሜ ነው፡፡ ቅጽል ደግሞ ስምን ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር የሚገልጽ ነው፡፡ለምሳሌ:- ከመጠን፣ ከባህሪ፣ ከሁኔታ፣ ከቀለም ወዘተ. ግስ የምንለው የአንድን ድርጊት መከናወን ወይም አንድ ነገር ካለመሆን ወደመሆን መምጣቱን ለማሳየት የሚገባ የአረፍተነገር መቋጫ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በየምድባቸው የተዘረዘሩ ቃላት ቀርበዋል፡፡ በጥሞና አስተውሉና ተመሳስሏቸውን ለመገንዘብ ሞክሩ፡፡

1. ሰው፣መሐመድ፣፣መጽሐፍ፣አዲስአበባ፣ዜና፣ ህልም፣ጠረጴዛ፣ሕዝብ... መጠሪያዎች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ስሞች ይባላሉ፡፡
2. አስተዋይ፣አሮጌ፣ወቅታዊ፣መጥፎ፣ትልቅ፣ታታሪ፣ቀይ...ቃላት ደግሞ የስም ገላጮች/ ቅፅሎች ይባላሉ፡፡
3. በላ፣ነዉ፣መከርከት፣ሰራ፣አገኘ፣ዘራ፣ናቸው...የሚሉት ቃላት የዓ.ነገሮች ማሰሪያዎች ሲሆኑ ድርጊትንና መሆንን ስለሚያመለክቱ ግሶች ይባላሉ፡፡
4. እዚህ፣ዛሬ፣ክፉኛ፣በፍጥነት፣እንደገና...የሚሉት ደግሞ ተውሳከ ግሶች ይባላሉ፡፡
5. ስለ-፣እንደ-፣እስከ-፣ወደ-፣ከ-፣...የመሳሰሉት መስተዋድዶች ናቸው፡፡
6. ምሳሌ:-<u>ከ</u> ሰው <u>ጋር</u>፣ <u>ስለ</u>ትምህርት ወዘተ

## ? መልመጃ-!

ሀ. የቀደመ እውቀታችሁን በመጠቀም ከላይ በቀረበው ምሳሌ መነሻነት ልዩ ልዩ የቃል ክፍሎችን ዘርዝሩ፡፡

1. ሥሞች፡- ____________፣____________፣_____________፣____________
2. ቅፅሎች፡-____________፣____________፣______________፣____________
3. ግሶች፡-____________፣____________፣_____________፣____________

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ክፍል ግለፁ፡፡

1. ሰነፍ ሰው ሰራን አይወድም፡፡____________
2. አየለ መኪና ገዛ፡፡_____________
3. መንኮራኩሯ ጨረቃ ላይ አረፈች፡፡____________
4. መጽሐፉን በፍጥነት መለሰ፡፡___________

## ክፍለ ትምህርት ሰላሳ አንድ

## ጥምር ቃላት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- ልዩ ልዩ ቃላትን በማጣመር(ድርብ በማድረግ) አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ፡፡

### ድርብ ቃላት

ሁለት የተለያዩ ቃላት ሲጣመሩ(አንድ ላይ ሲያያዙ) እንደ አንድ ቃል ያገለግላሉ፡፡

ምሳሌ፡- -ዓመትና በዓል ሲጣመሩ ዓመት በዓል፣

-ወጥ እና ቤት ሲጣመሩ ወጥቤት፣

-ትምህርትና ቤት ሲጣመሩ ትምህርት ቤት ወዘተ.ይሆናሉ፡፡

- የጥምር/ድርብ ቃል ጥቅሙ በአንድ ቃል መግለጽ የማይቻለውን ሐሳብ/ነገር ወይም እቃ ለመግለጽ ነው፡፡

# መልመጃ-፩

ሀ. ከሚከተሉት ቃሎች መካከል ድርብ/ጥምር ቃላት የሆኑትን ለይታችሁ አውጡና የተመሰረቱበትን ሁለት ልዩ ልዩ ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-ዳቦ ቤት= ዳቦ+ቤት

1. ጥሬ ስጋ
2. ደግ ስራ
3. ጥልፍልፍ
4. ወፍጮ ቤት
5. ወንድማማቾች
6. ቅርንጫፎች
7. ሹል አፍ
8. ልጃገረድ
9. ቤት ጠባቂ
10. ጸረ ሰላም

ለ. ከዚህ ቀጥሎ በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ክፍል ትርጉም ሰጥቶ ሊጣመሩ የሚችለውን በመምረጥ አዲስ ቃል ፍጠሩ፡፡

| "ሀ" | "ለ" | የተጣመረው ቃል |
|---|---|---|
| ሀ.ሐኪም | 1. መንበር | 1. ሐኪም ቤት |
| ለ.ሊቀ | 2. ቤት | 2.____________ |
| ሐ.የቤት | 3. አንጀት | 3.____________ |
| መ.ወተት | 4. አቀባይ | 4.____________ |
| ሠ.ላብ | 5. እመቤት | 5.____________ |
| ረ.ሥራ | 6. ሰራዊት | 6.____________ |
| ሰ.ጥቅል | 7. ጎመን | 7.____________ |
| ሸ.ሕዝባዊ | 8. አደር | 8.____________ |
| ቀ.ዓለም | 9. ጥገና | 9.____________ |
| በ.ቀዶ | 10. ፈት | 10.____________ |
| ተ.ሥራ | 11. አቀፍ | 11.____________ |
| ቸ.ቃል | 12. አስኪያጅ | 12.____________ |

# አስራ አንደኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰላሳ ሁለት

## ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ማዛመድ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የልዩ ልዩ ቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላትን ፍች ለይቶ ማዛመድ፡፡

### የጨለማ ጉዞ

አይኖቼ ክፍት ናቸው፡፡ እንዲያውም ሊቀደዱ እስኪደርሱ ድረስ ተበልጥጠዋል፡፡ ግን አያዩም፡፡ ቢያዩም የጠቆረ አየርን ነው፡፡ ሌላ ነገር የለም፡፡ ይሁን እንጂ ስንቱ ነገር በጨለማ ተሸፍኖ ይገኛል፡፡

በስሜት ተሳቢዎች የሚባሉት የዱር አራዊትና ጨለማ የለበሱ ወንበዴዎች የምድር ተሳቢዎች እንደሚገኙ የጨለማ ተጓዥ ይገነዘባል፡፡ ግን አያያቸውም፡፡ ባለማየቱም እነኚህ ነገሮች የሉም ከሚለው ይልቅ አሉ የሚለውን ሀሳብ አጥብቆ ይይዛል፤ይጓዛልም፡፡



ነፋስ በዛፎች መካከል ሽው ብሎ ሲያልፍ የዛፉን ቅጠሎች ያጋጫቸዋል፡፡ አንዲት ደረቅ ቅጠልም ስትወድቅ ኮሽ የሚል ድምፅ ትሰጣለች፡፡ ተጓዥ ባለበት ስፍራ ድንግጥ ብሎ ይቀራል፡፡ ደሙ ቀዝቀዝ ብሎ በድን ይሆናል፡፡ ጥቂት ቆየት ብሎ ልቡ ቷቷ!...ቷቷ! ስትል ነፍስ ይገዛል፡፡ ግን ይንቀጠቀጣል፡፡ ምን ድምፅ ነበር የሰማሁት? ማነው ያንኮሻኮሸው? ወንበዴ? ጅብ? በማለት ራሱን እየጠየቀ ሲጓዝ ሌላ ቅጠል አጠገቡ ተመሳሳይ ድምፅ በመስጠት ትወድቃለች፡፡ ውይ! ለካ ቅጠል

ነው አይ የጨለማ ጉዞ! ለስላሳ መንገድ ነው ብሎ እንደልቡ መራመድ ሲጀምር በድንገት አንዲት ድንጋይ አውራ ጣቱን ትመታዋለች፡፡ ተንደርድሮ ዘፍ ይላል፡፡ አወዳደቁ በጨለማ ግዛት ውስጥ ስለሆነ የቦንብ ፍንዳታ የመሰለ ድምጽ ይሰጣል፡፡ ምንጭ፡-( አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማን አህሎት ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው? ፣ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1992ዓ.ም፣106-110)

## ? መልመጃ:- !2

ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ በፍች የሚመሳሰላቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ሊቀደዱ | ሀ.ክልል |
| 2. መራመድ | ለ.ውልብ |
| 3. በስሜት | ሐ.መሄድ |
| 4. የሰማሁት | መ.ሊሰነጠቁ፣ሊሸነቆሩ |
| 5. ግዛት | ሠ.በሀሳብ |
| 6. ሽው | ረ.ያዳመጥኩት |
| 7. አየር | ሰ.ሬሳ |
| 8. በድን | ሸ.አካባቢ |
| 9. ስፍራ | ቀ.ነፋስ |

ለ. ቀጣዮቹ ቃላት ምንባቡን መነሻ ያደረጉ ናቸው፡፡በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ከ"ለ" ክፍል በትርጉም ተቃራኒ የሆነውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ጨለማ | ሀ.እርጥብ |
| 2. ደረቅ | ለ.በሩቁ |
| 3. አጠገቡ | ሐ.ብርሐን |
| 4. አወዳደቁ | መ.ያረጋጋቸዋል |
| 5. ለስላሳ | ሠ.ተከድነዋል |
| 6. ተበልጥጠዋል | ረ. ከርዳዳ |
| 7. አጥብቆ | ሰ. አረማመዱ |
| 8. ያጋጫቸዋል | ሸ.አላልቶ |
| | ቀ.ድምፅ |

# ክፍለ ትምህርት ሰላሳ ሶስት

## አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት

### የክ/ትምህርቱ አላማ

- አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት መጠቀም፡፡

## አያያዦችና የመሸጋገሪያ ቃላት

አያያዥ እና የመሸጋገሪያ ቃላት በብዙ ዓ.ነገሮች የሚገልጹ ሀሳቦች እርስ በርስ ተቀናጅተውና ተዋህደው እንዲቀርቡ የሚያግዙ ቃላት ናቸው፡፡አያያዦች ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ቅጥያዎች እና ሐረጋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አገልግሎታቸውም በዓ.ነገር፣በአንቀጽ ወይም በድርሰት ውስጥ እየተገኙ የሀሳቦችን ውህደትና ጥምረት መፍጠር ነው፡፡ ከአንዱ ሐሳብ ወደ ሌላው ሐሳብም ያሸጋግራሉ፡፡

አያያዦችና የመሸጋገሪያ ቃላት በርካታ ናቸው፡፡የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እና፣ ግን፣ሆኖም፣እርግጥ፣እንጂ፣ ስለዚህ፣ያህል፣እንደገና፣ የሆነው ሆኖ...፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ.አበበ ተማሪና ነጋዴ ነው፤ይሁን እንጂ፣በሁለቱም ውጤታማ አይደለም፡፡

-እና፡-ሐረግን ከሀረግ

-ይሁን እንጂ፡-ዓ.ነገርን ከዓ.ነገር አያይዟል፡፡

ለ.የተዘረዘሩ ዓ.ነገሮች በአያያዥ ቃላት ተያይዘው ሲቀርቡ፡-

- የሰው ልጅ ለምግቡ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- የሰው ልጅ ለልብሱ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- የሰው ልጅ ለመጠለያ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- የሰው ልጅ ለምግቡ፣ለልብሱ እንዲሁም ለመጠለያው ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- እንዲሁም፡- ሐረግን ከሐረግ አያይዟል፤ሀሳቡንም አቅልሎታል፡፡

# መልመጃ-፲

## ሀ. ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ አያያዥችንና የመሸጋገሪያ ቃላትን/ሐረጋትን አውጡ፡፡

ክረምት የዝናብ ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ተክል ርጥበት ይሰማዋል፤ለምለም ሆኖ ይታያል፡፡ ዳሩግን በበጋው ወራት ሙቀቱ ለምለም የነበረውን ተክል ብዙ ድርቅ ይሰማውና ይጠወልጋል፡፡ አንዳንዱም ጨርሶ ይጠፋል፡፡ በክረምቱ ወራት በጣም ይበርዳል፤በበጋ ግን ሙቀቱ ሀይለኛ ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ክረምቱ ለበጋው በጋው ለክረምቱ ተቃራኒ ስለሆነ ነው፡፡

## ለ. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች በተስማሚ ዓ.ነገሮች አጣምሩ፡፡

ምሳሌ፡- -ውድድሩ ከባድ ነው፡፡

-ማሸነፋችን አይቀርም፡፡

*ውድድሩ ከባድ ቢሆንም ማሸነፋችን አይቀርም፡፡

1) -የነገርኩህ ይጠቅምሃል፡፡

-አይጎዳህም፡፡

2) -ትያትሩ ጥሩ ነበር፡፡

-ገንዘብ የለኝም፡፡

3) -ትምህርት ጥሩ ነው፡፡

-ስራ ላይ ካልዋለ እርባና የለውም

4) -ሐሳቡ አይገባኝም፡፡

-ከማጥናት አልቆጠብም፡፡

5) -ደጋግሜ መክሬዋለሁ፡፡

-እንደፈለገ ይሁን፡፡

6.-ባለቀለም ቴሌቭዥን እወዳለሁ፡፡

-ለመግዛት አቅም የለኝም፡፡

7.-ፊልሙን እወደዋለሁ፡፡

-ለማየት አልቻልኩም፡፡

8.-ምሳህን ብላ፡፡

-ተያይዘን መርካቶ እንሄዳለን፡፡

9.-ለመምጣት ወስኜ ነበር፡፡

-ሳይመቸኝ ቀረ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሰላሳ አራት

## አንቀጽ መጻፍ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- በተመረጡ ርዕሠ ጉዳዮች ዙሪያ ነጠላ(አንድ) ሀሳብን ብቻ የያዙ ሐሳቦችን ወይም የተዘበራረቁትን ዓ.ነገሮች አቀናጅቶ አንቀጽን መጻፍ፡፡

**ማስታወሻ**

አንቀጽ፡- ማለት በአንድ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ብቻ የሚያተኩር የዓ.ነገሮች ስብስብና የድርሰት መመስረቻ አካል ነው፡፡

## ? መልመጃ፡- !4

ሀ. ከዚህ በታች ተዛብተው ያሉትን የተለያዩ ዓ.ነገሮች አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላትን/ ሀረጋትን በመጠቀም የሀሳብ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቃችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡

1. አበበ ከመኝታው በጠዋት ተነሳ፡፡
2. እጁን ታጥቦ ቁርሱን በላ፡፡
3. ደብተሩን አዘጋጀ፡፡
4. ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደ፡፡
5. ልብሱን ለበሰ፡፡
6. ከዝያም ወደ ትምህርት ቤት ሔደ፡፡

1. ከዝያም እቤት እቤታቸው ገብተው ከረጢቶቻቸውን በመያዝ ዶቅማ ለመልቀም ወደ ወንዝ ይወርዳሉ፡፡
2. በሜዳው ላይ ተሰበሰቡ፡፡
3. ፉጨቱን ሰምተው የሰፈሩ ልጆች፤
4. ሁሉም በጠዋት ተነስተው ያገኙትን ቁርስ አደረጉ፡፡
5. ልክ ሰዓቱ ሲደርስ፤

ለ. ቀጥለው ከቀረቡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ። እርስ በርስም በማስተያየት ሀሳብ ተለዋወጡ።

1. የትምህርት ቤት ጓደኛዬ
2. የእናቴ ናፍቆት
3. ትንሿ ጎጇችን
4. ትምህርት ቤት ሲከፈት
5. የክረምት ወቅት

# አስራ ሁለተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰላሳ አምስት

### አንብቦ መረዳት(ተረት ተረት)

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- ቀለል ያሉ ሥነ-ጽሑፎችን(ተረትና ምሳሌን) በማንበብ የንባብ ክሒልን ማሳደግ።

## ተረትና ምሳሌ

በአንድ ቤት ውስጥ አባትና ልጆች አብረው ይኖሩ ነበር። አባትዬው ታድያ ሁል ጊዜ በልጆቹ አለመስማማት ይጨነቅ፣ይጠበብ ነበር። ልጆቹም አራት ሲሆኑ አባታቸው ገበሬ ነበር። ልጆቹ በእረኝነት ተግባር አባታቸውን ያገለግሉ ነበር። በእረኝነት በሚሰማሩበት ጊዜ በሕብረት ሆነው ሳይሆን የተናጥል ስራ ነበር የሚሰሩት። አንደኛው ከብቶቹን ወደዚያ እወስዳለሁ ሲል ሌላኛው ደግሞ አይሆንም አይሄዱም ይላል። በዚህ አይነት ሁሌ እንደተጨቃጨቁ፣ እንደተነታረኩ፣ እንደተጋጩ ይውላሉ። ቀን ላይም አንደኛው እኔ ነኝ ከብቶቹን የማጠጣው ሲል ሌላኛው ደግሞ እኔ ነኝ እንጂ አንተ አታጠጣም፣ አንተ ወደ ወንዝ አትወስዳቸውም በማለት ይጣላሉ፣ይደባደባሉ። አባታቸው በዚህ ሁኔታ በእጅጉ ይበሳጭ ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን አባት ልጆቹን በሙሉ ሰብስቦ ጠራና ቀጫጭን እንጨቶችን እንዲሰበስቡ ለሁሉም ነገራቸው። እነርሱም ሰብስበው አቀረቡለት። ከዚያም እነዚህን ጭራሮች አጥብቀው እንዲያስሩ ነገራቸው። ከዝያም የታሰረውን ጭራሮ ለሰበረ ሽልማት እሰጣለሁ አላቸው። እነርሱም በየተራ የታሰሩትን ጭራሮች ለመስበር

ሞከሩ፤ግን አንዳቸውም መስበር አልቻሉም። ይህን የተመለከተው አባት እንዲህ አላቸው፤“ተመልከቱ! እነዚህን ጭራሮች አንዳችሁም ለመስበር አልቻላችሁም። እስቲ እስሩን ፍቱትና እያንዳንዱን ጭራሮ ስበሩት” አላቸው። ልጆቹም ጭራሮቹን ወይም እንጨቶቹን አንድ በአንድ እያነሱ በቀላሉ ሰበሯቸው። አባታቸውም እንዲህ አላቸው“ ልጆቼ አያችሁ‘ድር ቢያብር አንበሳ ያስር’ እንደሚባለው አንድነት ጥንካሬ ነው። አንድ ብትሆኑ እናንተም ተባብራችሁ በመሃላችሁ ጥልና ጭቅጭቅ ባይኖር ትጠነክራላችሁ፤ጠላታችሁም አይደፍራችሁም። ስለዚህ አንድ ሁኑ!፤ተባበሩ፤አትጣሉ” አላቸው። ልጆቹም የአባታቸውን ምክር ተቀብለው ይቅርታ ተጠያይቀው የተዘጋጀውን ሽልማት አባታቸው ለአራቱም ልጆች ሰጥቶ ሸኛቸው።

## ? መልመጃ:- !5

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ።**

1. ሽልማት ያዘጋጀው ሰው ማን ነው?
2. በቀረበው ታሪክ ውስጥ ስንት ሰዎች ተካፍለዋል?
3. አባታቸው ለምን ይበሳጭ ነበር?
4. የጽሑፉ አጠቃላይ መልዕክት/ሐሳብ ምን ይመስላችኋል?

**ለ. ምንባቡን መነሻ በማድረግ ቀጥለው በ“ሀ” ክፍል ለቀረቡት ቃላት በሀሳብ(በፍች) የሚዛመዷቸውን ከ“ለ” ክፍል በመምረጥ አዛምዱ።**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሁል ጊዜ | ሀ.በጠባቂነት |
| 2. ይጨነቅ | ለ.ዘወትር |
| 3. በእረኝነት | ሐ.የግል |
| 4. የተናጥል | መ.ያስብ |
| 5. በእጅጉ | ሠ.ምህረት |
| 6. ሽልማት | ረ.ስጦታ |
| 7. ይቅርታ | ሰ.ሕብረት |
| 8. ጥንካሬ | ሸ.ተግሳፅ |
| 9. አንድነት | ቀ.ሐይል |
| 10. ምክር | በ.በብዙ |

# ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት

# ምዕራፍ ስድስት

# ሥነ ቃል

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የሥነ ቃልን ምንነት፣ዓይነትና አገልግሎት ትለያላችሁ፤
- የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያን ታዳምጣላችሁ፤ትተገብራላችሁ
- የማህበራዊ መስተጋብሮችና መተሳሰሮች ግንኙነት ሁኔታዎችን ትናገራላችሁ፤
- በጉብኝት ጊዜ ስላያችሁት/ስለተመለከታችሁት፣ ስለታዘባችሁት ጉዳይ ትናገራላችሁ፤
- ተግባራቱን ለመስራት መመሪያዎችን ታነባላችሁ፤
- በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ትፅፋላችሁ፤
- አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ሐረጎችንና ዓ.ነገሮችን ትፅፋላችሁ፤
- በሚቀርበው ጽሑፍ መሰረት ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም ትሰጣላችሁ፤
- የቃል ክፍሎችን ታስረዳላችሁ፡፡

# አስራ ሶስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አርባ

### ሥነ ቃል

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ፡**

- የስነ ቃልን ምንነት፣አይነትና አገልግሎት መለየት፡፡

ሥነ-ቃል በመነገር፣በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከናወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን፣የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ልማድ፣እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችና የሕይወት መልኮችን መግለጫ ኪነ ጥበብ ነው፡፡

ይህ ኪነ-ጥበብ ማሕበረሰቦች በረዥም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅረስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞችም ማንጸባረቂያ ነው፡፡

ይህ ቃላዊ ኪነ ጥበብ በተለይ ፊደል ቀርፀው በጽሑፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትና ምንነት፣ እምነትን የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን በአጠቃላይ የአለም አመለካከትን ቀረፃ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በሥነ ቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል፤የዝርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል፤ስለአካባቢያቸውና በአጠቃላይ ስለማንነታቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርፁበታል፡፡ ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋንኛ መሳሪያቸው ነው፡፡ ሀዘንደስታቸውን፣ምኞት ተስፋቸውን፣ፍቅር ጥላቻቸውን፣ድል ሽንፈታቸውን፣ድጋፍ ተቃውሚቸውን፣በአጠቃላይ የሕይወታቸውን መልኮች ያንፀባርቁበታል፡፡ ታሪካቸውን ለተከታዮቻቸው በማስተላለፍ የዝርያቸውን ተከታታይነት ያረጋግጡበታል፡፡ ሰናይ የሚሏቸውን ማህበራዊ እሴቶችና ልማዶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ እኩይ የሚሏቸው ደግሞ እንዲወገዱ ያደርጉበታል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች፣የተፈጥሮ አደጋ፣ ስደት፣ርሃብ፣ወረርሽኝ፣ጦርነት የመሳሰሉት

ኑሮን አናጊ አጋጣሚዎች ሲደርሱ በሥነ ቃል ይገለፃሉ፤ይታወሳሉ፤ማህበረሰቡ ለእነዚህ አስከፊ አጋጣሚዎች የነበረው አመለካከትና የደረሰበት ጉዳት በሥነ-ቃሉ አማካይነት ተቀርጾ ለተከታዩ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

የሥነ ቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው፡፡ በተለይ ጥንታዊ የአኗኗር ዘይቤ ባልተራቀቁና ባልበለፀጉ ማህበረሰቦች በእለት ተዕለት ሕይወታቸው ውስጥ በሚከሰቱ የተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያት አያሌ ስነ ቃሎች ይፈጠራሉ፡፡

በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በየወቅቱና በየዘመናቱ የሚወሩት ተረቶች፣ በአምልኮ ስነ-ሥርዓቶች ላይ የሚደረደሩ ውዳሴ አማልክትና ዝማሬዎች፤ በእርሻ፣ በአረም፣በአጨዳና በውቂያ በሌሎችም መሰል ሕይወት ደጋፊ ሥራዎች ላይ የሚዜሙና የሚነገሩ ስነቃሎች ማህበረሰቦቹ ስለራሳቸው፤ስለሰው ልጅ፤ ስለአካባቢያቸውና ስለዓለም ያሏቸውን አመለካከቶችና የሕይወት ፍልስፍናዎች የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

ምንጭ፡-ዘሪሁን አስፋው፣"የስነ ጽሑፍ መሰረታውያን"፣1992ዓ.ም

## ? መልመጃ፡-፫6

፩. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በቃል ግለጹ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. የሚከሰት | ለ.መስተጋብር | ሐ.ጥርቅም | መ.አናጊ |
| ሠ.ትግል | ረ. የሕይወት | ሰ.ሚና | ሸ.ያሳውቁበታል |

2.በምድብ"ሀ" የቀረቡትን ቃሎች በምድብ "ለ" ከተዘረዘሩት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አያሌ | ሀ.መልካም |
| 2. ምንጭ | ለ.ይነገራሉ |
| 3. ሰናይ | ሐ.ብዙ |
| 4. ይፈጠራሉ | መ.ብርቱ |
| 5. ሚና | ሠ.መነሻ |
| | ረ.ድርሻ |

ፗ:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ::

1. ማንኛውም ጽሑፍ በመተረት ወይም በመዜም በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ነው::
2. የስነቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው::
3. ስነቃል በጥንታዊ ማህበረሰቦች ውስጥ አይገኝም::
4. ማህበረሰቡ እኩይ የሚሏቸው ማህበራዊ እሴቶች መወገድ የለባቸውም::
5. ስነቃል በቃልና በጽሑፍ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል::

## ክፍለ ትምህርት አርባ አንድ

## የቤተ መጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን አዳምጦ ተግባራዊ ማድረግ::

### መልመጃ:- !7

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ“እውነት” ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት በጽሁፍ መልሱ::

1. ቤተመጻሕፍት መፃህፍት ብቻ የሚገኙበት ስፍራ ነው::
2. በቤተመጻሕፍት ውስጥ ሥነ-ስርዓት መጠበቅ መሰረታዊ ነገር ነው::
3. ያለመታወቂያ ከቤተመጻሕፍት መፅሐፍን መዋስ ይቻላል::
4. የመጻሕፍት መለያ ካርዶች የሚዘጋጁት በፊደል ወይም በቁጥር ነው::

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አራት አራት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል:: ከቀረቡት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን አማራጭ መርጣችሁ ጻፉ::

1. በቤተመጻሕፍት ውስጥ የራስን_______________ይዞ መግባት አይፈቀድም::

   ሀ.እርሳስ ሐ.መጽሐፍ

ለ.ደብተር መ.ብዕር

2. በቤተመጻሕፍት ለማንበብ የምንፈልገውን መፅሐፍ ለይተን ካወቅን በኋላ ለቤተመጻህፍቱ ሠራተኛ የምንሰጠው_________________ነው፡፡

ሀ.የደራሲው ስም መለያ፤

ለ.የአሳታሚው ድርጅት ስም መለያ፤

ሐ.የመታወቂያ ካርድ፤

መ.የመጽሐፉን ርዕስ መለያ፤

3. "ሥነ-ስርዓት ማክበር!" የሚለው ሀሳብ የሚያካትተው ወይም የሚይዘው________________የሚለውን ነው፡፡

ሀ.በመጽሐፉ ላይ አለመጻፍን፤

ለ.መጽሐፍ አለመቅደድን፤

ሐ.በፀጥታ ማንበብ፤

መ.ሁሉም መልስ ነው፡፡

## ክፍለ ትምህርት አርባ ሁለት

## እርስ በርስ መረዳዳት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- ልዩ ልዩ ማህበራዊ መስተጋብሮችን መነሻ በማድረግ ጭውውት ማድረግ፡፡

## ? መልመጃ:- ፬8

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. በሰዎች መካከል የሚደረገው የእርስ በርስ መረዳዳት ምን ጠቀሜታ የሚያስገኝ ይመስላችኋል?

ለ. ከጓደኞቻችሁ ጋር እንዴት ትረዳዳላችሁ

# ምንባብ

እድር ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚቋቋም የመረዳጃ ማህበር ነው፡፡ ሰዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በሀዘንና በሌሎች ችግሮች ጊዜ ለመረዳዳት እድር ይመሰርታሉ፡፡ ወይዘሮ ኡፋይሴና አቶ አንጃ በአንድ አካባቢ ይኖራሉ፡፡ የሰፈራቸውም እድር አባል ናቸው፡፡ ዕለቱ እሁድ በመሆኑ ሁለቱም የእድር ክፍያ ለመክፈል ሲሄዱ በመንገድ ላይ ተገናኝተው ስለ እድራቸው ይወያያሉ፡፡



አቶ አንጃ፡- “ወይዘሮ ኡፋይሴ እንደምን አረፈድሽ? ምነው የመስቀል ወፍ ሆንሽ? አይቼሽ አላውቅም፣በሀገር አልነበርሽም?”

ወ/ሮ ኡፋይሴ፡- “ኧረ አለሁ፡፡ ሰሞኑን ትንሽ አሞኝ ስለነበር ከቤት ወጥቼ አላውቅም፡፡ አንተ ደህና ነህ?”

አቶ አንጃ፡- “እኔ ደህና ነኝ፤መታመምሽንኮ አልሰማሁም፡፡ ብሰማ ኖሮ እጠይቅሽ ነበር! ምን አሞሽ ነበር?”

ወ/ሮ ኡፋይሴ፡- “ያው የተለመደው ተነስቶብኝ ነው፡፡ ሥራ መስራት ከለከለኝ፤ጾም አዳሪ አደረገኝኮ!”

አቶ አንጃ፡- “ነው እንዴ! አዲስ በሽታ መስሎኝ ነው፡፡ አይዞሽ! ሀኪም የሚያዝልሽን መድሐኒት ውሰጂ፤ምግብ ተመገቢ!”

ወ/ሮ ኡፋይሴ፡- “እሺ እወስዳለሁ፡፡ ብቻ እጅ አጠረኝ፣እንዲያው ይኼ እድር ምናለ ትንሽ ገንዘብ ለህክምና ቢያግዘኝ? ባለፈው ለተቸገሩ ብዙ ሰዎች ድጋፍ አደረገ ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ ለእኔም ለምግብና ለህክምና የሚሆን ትንሽ ገንዘብ ይተባበረኝ ይሆን?”

**አቶ አንጃ:-** “አዎ የተቸገሩ ሰዎችን እድራችን እየረዳ ነው፡፡ በቅርቡ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህፃናትን፣አረጋውያንንና የተቸገሩ ሰዎችን ለይቶ በመመዝገብ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል፡፡ አንቺምኮ ተመዝግበሻል!”

ወ/ሮ ኡፋይሴ:- “እኔስ መመዝገቤንም አላወቅሁም፡፡ እባክህ ከቻልክ በሰፈር ተወካይነትህ ኮሚቴዎችን አሳስብልኝና እኔም የተወሰነ ድጋፍ እንዳገኝ እርዳኝ!”

**አቶ አንጃ:-** “እሺ! ያው ድጋፍ የሚሰጠው እንደችግሩ ክብደት ነው፡፡ የአንቺ ደግሞ የጤና ችግር ስለሆነ ድጋፉን ታገኛለሽ ብዬ እገምታለሁ፡፡ ለማንኛውም እኔም ያንቺን ጉዳይ አቀርብልሻለሁ፡፡ አይዞሽ በርታ በይ!”

ወ/ሮ ኡፋይሴ:- “ይበጅህ አቶ አንጃ! እኔማ ጧሪ ቀባሪ ልጅ የለኝ፣አንድ እድሬን አምኜ አይደል የምኖር፡፡”

**አቶ አንጃ:-** “ለሁላችንም ቢሆን በችግር ጊዜ ለመረዳዳት ተስፋችን እድራችን እኮ ነው! በሀዘን ጊዜም ሆነ የከፋ ችግር ሲያጋጥም መረዳዳት የምንችልበት ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንባችን ላይ ሰፍሯል፡፡ እድርኮ ለማህበራዊ ግንኙነታችን መሰረት በመሆኑ ለችግራችንም ጊዜ አለኝታችን ነው፡፡”

ወ/ሮ ኡፋይሴ:- “ልክ ነህ አቶ አንጃ፡፡ በእድሩ ምክንያት ከብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቄያለሁ፡፡ ብዙዎቹም እየረዱኝ ነው፡፡ ይህ እድር ባይኖር ምን ይውጠኝ ነበር?”

**አቶ አንጃ:-** “ልክ ነሽ፡፡ በእድሩ ምክንያት ጉርብትናን፣መተሳሰብንና ፍቅርን አጎልብተናል፡፡ በተለይ በሀዘን ጊዜ ሀዘንተኛውን ለማፅናናት ከግል ይልቅ በጋራ መሆኑ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ለማንኛውም አሁን እየደረስን ስለሆነ ያለሽን ችግር ለዕድሩ አባላት አንቺም እኔም እናቅርብና የሚሰጥሽን ድጋፍ በመቀበል ህክምናሽን ትከታተያለሽ፤አይዞሽ!”

ወ/ሮ ኡፋይሴ:-“እሺ አቶ አንጃ በጣም አመሰግናለሁ”

## 2.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

ሀ.ሰዎች እድር የሚያቋቁሙት ለምንድነው?


ለ.ወ/ሮ ኡፋይሴ ከእድሩ እርዳታ የሚያገኙ ይመስሏችኋል?ለምን?

ሐ.የእድሩ አባላት መተዳደሪያ ደንብ ያወጡት ምን ሊያደርጉበት ነው?

መ.የእድር አባል መሆን የሚችሉት በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ናቸው? ለምን?

ሠ.በአካባቢያችሁ የተቋቋሙ እድሮች በምንባቡ ከተገነዘባችሁት እድር ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት አብራሩ፡፡(በቡድን ተነጋገሩበት)

፫.የአካባቢያችሁን ማህበራዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ የተከበቡትን ቦታዎች በትክክል አሟሉ።




## አስራ አራተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አርባ ሶስት

### የጉዞ ዘገባ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- በአካባቢ የሚገኝ አንድ ቦታ ጉብኝት ዘገባ(ሪፖርት) ማዘጋጀትና ማቅረብ።

## ማስታወሻ

- ዘገባ ማለት አንድ የተወሰነ ክንውንን(ተግባርን) በመመልከት፣በማንበብ... ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለሌሎች እንደማስረጃ ጽፎ/አደራጅቶ ማቅረቢያና የመረጃ መለዋወጫ መንገድ ነው፡፡
- ከዋና ዋና የዘገባ አይነቶች መካከል:-

1. የመስክ/የጉዞ ዘገባ
2. የንባብ ዘገባ
3. የማስታወሻ ዘገባ እና
4. የምርምር ዘገባ
5. ሒደታዊ ዘገባ ይጠቀሳሉ፡፡

## ምሳሌ፡-

✅ የጉዞ ዘገባ(የጉብኝት)

ቀን_______________

የዘገባ አቅራቢ:-የ5ኛ"ሀ" ክፍል ተወካይ

የዘገባው አላማ:-የዕውቀት ፋና ት/ቤት ጉብኝትን ለአጅራ ት/ቤት ማሳወቅ፡፡

ካለንበት ትምህርት ቤት 2፡30 በመኪና ከተጓዝን በኋላ በ4፡30 እውቀት ፋና 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ደረስን፡፡የእውቀት ፋና ተማሪዎች በሰልፍ ቆመው ተቀበሉን፤ ከዚያም ከመካከላቸው አንዱ ት/ቤቱን ያስጎበኘን ጀመር፡፡

የትምህርት ቤቱ ግቢ በእፅዋትና በባህር ዛፎች የተከበበ ነው፡፡ወደ ት/ቤቱ ዘልቀው ሲገቡ ግራና ቀኝ የተከረከሙ ጽዶች ይታያሉ፡፡ በረዥም እንጨት ላይ የሚውለበለበው የኢትዮጵያ ባንዲራ ከሩቅ ይታያል፡፡

የዕውቀት ፋና ት/ቤት 20 የመማሪያ ክፍሎች፤አንድ የርዕሠ መምህር ቢሮና የመምህራንና የተማሪዎች መዝናኛ ክፍሎች አሉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች የሚያጠኑበት መለስተኛ ቤተመጻሕፍትና መጸዳጃ ቤቶችም አሉት፡፡

ክፍሎቹ የተሰሩት በሁለት ረድፍ ሲሆን በሁለቱም ረድፎች አስር የመማሪያ ክፍሎች አሉት፡፡ ሁሉም የተገነቡት በብሎኬት ነው፡፡ የውስጥ ግድግዳቸው ሰማያዊ ቀለም የተቀባ ሲሆን ወለሉ ሲሚንቶ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ 45 አግዳሚ

ወንበሮችና ሀያ ጠረጴዛዎች ይገኛሉ፡፡ በእያንዳንዱ አግዳሚ ወንበር ላይ ሶስት ተማሪዎች ይቀመጣሉ፡፡

የዕውቀት ፋና ት/ቤት ተማሪዎች ሁል ጊዜ በየተራ ክፍሉን ያፀዱታል፡፡ ስለዚህ በክፍሉ ውስጥ ምንም ዓይነት ቆሻሻ አይታይም፡፡ በክፍሎቹ በራፍ አካባቢም የሚያማምሩ አበባዎች ተተክለዋል፡፡እነሱንም ተማሪዎች በየተራ ውኃ ያጠጧቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሳምንቱ መጨረሻ በክበባቸው አማካይነት ውይይትና ክርክር ያቀርባሉ፡፡ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ሲወያዩ ያስደስታሉ፡፡ በውይይታቸው ወቅት ስለ ት/ቤታቸው እድገት የተለያዩ ሀሳቦችን ያፈልቃሉ፡፡ ተማሪዎች መምህሮቻቸውን ያከብራሉ፤መምህራንም ተማሪዎቹን ይወዷቸዋል፡፡ ስለዚህ የእውቀት ፋና ት/ቤት የሚወደድ ነው፡፡

ጉብኝታችንን በ7፡30 አጠናቀን ወደመጣንበት ስፍራ ተመለስን፡፡ እኛም ከዚህ ት/ቤት ብዙ ትምህርት አግኝተናል፡፡ስለዚህ ትምህርት ቤታችንን ተወዳጅ ለማድረግ ጠንክረን እንሰራለን፡፡

## ? መልመጃ- !9

ከላይ በቀረበላችሁ ምሳሌ መሰረት በአካባቢያችሁ የሚገኝን አንድ የችግኝ ጣብያ በቡድን ጎብኝታሁ ወይም የጣቢያውን ኃላፊ ጠይቃችሁ ቀጣዩን ቅጽ ሞልታችሁ በማደራጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ቀን____________

ዘገባ አቅራቢ____________________________

የዘገባው ዓላማ________________________________

የችግኝ ጣቢያው ኃላፊ__________________________ይባላሉ፡፡

የችግኝ ማፍያ ቦታ አመራረጥ_________________________

የችግኝ መደብ አሰራር_______________________________________

አዘራር________________________________________________

የችግኝ መትከያ ከረጢት አዘገጃጀት____________________________

ለችግኝ የሚያገለግል የዳስ/ጥላ/ አሰራር_________________________

____________________________________________________________
የተባይ ወይም የአረም ማጥፊያ መድሐኒት______________________
የሚተከሉት ችግኞች አይነት__________________________________
ችግኞቹ በሚተከሉበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች
____________________________________________________________
____________________________________________________________
ለችግሮቹ መፍትሔዎች______________________________________
ከዘገባው አላማ አኳያ ለመንገር/ለማሳወቅ የተፈለገው ነገር__________

# ክፍለ ትምህርት አርባ አራት

## “የሕዝብ ብዛት”

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የማስታወሻ አያያዝ መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## የማስታወሻ አያያዝ መመሪያ

ማስታወሻ መያዝ አንድን ፍሬ ሀሳብ እንዳይዘነጋ ለማድረግና በቅርስነት ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡ ማስታወሻ መያዝ የሚያስፈልገው አንድ ንግግር ወይም ጽሑፍ ሲነበብ በምናዳምጥበት ጊዜ፣በጉብኝት ጊዜ፣ገለጻ ሲሰጥ ወይም አንድን ፅሁፍ በግል ስናነብ ነው፡፡ስለሆነም ወረቀትና ብዕር መያዝ ዋና ዋና ሀሳቦችን ወይም መረጃዎችን በቅደም-ተከተል መያዝና የተያዘውን ነገር ሳያጋንኑ ማጠናከር/አጠቃሎ መፃፍ/ ተገቢ ነው፡፡

በሀገራችን የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከመሬቷ የሚመረተው የምግብ ሰብል ከህዝቧ ብዛት ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ሰዎች ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሯቸውን ለሟሟላት ሲሉ ደን ለበስ መሬቶችን ይመነጥራሉ፡፡ ከፍተኛ ተዳፋትነት ያላቸውን ቦታዎች ያርሳሉ፡፡ ለተፈጥሮ ሀብት መመናመንም አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘላቂነት ባለው ስልት መጠቀም የኢኮኖሚ ልማትን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማካሄድ ስለሚያስችል ህብረተሰቡ አሁን ከተቆራኘው

ድህነት፣ረሃብ፣እርዛትና በሽታ ሊላቀቅ ይችላል፡፡ የሕብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ሲሻሻል ያለዕድሜው በተለያዩ ስራዎች እየተጠመዱ ከትምህርት የሚገለሉ ታዳጊ ህፃናት የተሻለ የትምህርት ዕድል የሚያገኙበትና የተሻለ ሕይወት ሊኖሩ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ይቻላል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ለማሟላት ህብረተሰቡ የተፈጥሮ ሀብቶችን በተገቢው መንገድ ለመጠበቅና ለመጠቀም እንዲሁም ቤተሰብን ለመመጠን የሚያስችሉ መንግስታዊ ፕሮግራሞችን መደገፍና ቀና ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

## ? መልመጃ-"

ሀ.ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ የህዝብ ብዛት ከሚለው ምንባብ ውስጥ በየአንቀጹ ያሉትን ዋና ዋና ሀሳቦች አውጥታችሁ በመጻፍ ከክፍል ጓደኞቻችሁጋር ተወያዩ፤

ምሳሌ:- የመጀመሪያው አንቀጽ ዋና ሀሳብ/ፍሬ ነገር:- ደኖችን መጨፍጨፍ ወይም ተዳፋት መሬቶችን ማረስ ለተፈጥሮ ሀብት መባከን አንዱ ምክንያት ነው የሚል ነው፡፡

ለ.ስለአንድ ስለሰማችሁት አስደሳች ወይም አሳዛኝ ነገር ቅደም-ተከተሉን የጠበቀ ማስታወሻ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሐ.የሚከተሉት ጥያቄዎች የህዝብ ብዛት ከሚለው ምንባብ የወጡ ናቸው፤ ጥያቄዎቹን አንብባችሁ በተሟሉ ዓ.ነገሮች በቃል መልሱ፡፡

1. በአካባቢያችን ለተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምክንያት የሆኑት ምን ምን ናቸው?
2. የተፈጥሮ ሀብቶች የምንላቸው የትኞቹ ናቸው?
3. የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘላቂነት ባለው ስልት መጠቀም የሚቻለው በምን አይነት መንገድ ነው?

# ክፍለ ትምህርት አርባ አምስት

## መጠይቃዊ ቃላት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ልዩ ልዩ ዓ.ነገሮችን መመስረት።


## ? መልመጃ፡-"፩

፩. በሚከተሉት ክፍት ቦታዎች መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም ዓ.ነገሮቹን አሟልታችሁ ፃፉ።

ሀ.የዚህ ግጥም ደራሲ____________ነው?
ለ.የእርሻ ግጥም________________ይከወናል?
ሐ.ገነት ሻንጣ ገዛች__________________?
መ.ስለሥነቃል__________________ታውቂያለሽ?
ሠ.የቀረርቶና የፉከራ ግጥም_____________ይጠቅማል?
ረ.ልብስህን አጠብክ_____________________?
ሰ.ዶሪ_______________________ሄደ?

2. ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምሳሌው መሰረት ስድስት መጠይቃዊ ዓረፍተ-ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡-



# አስራ አምስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አርባ ስድስት

### አያያዥ ቃላት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

✅ አያያዥ ቃላትን በሐረግና ዓ.ነገር ውስጥ በማስገባት ምስረታ ማድረግ፡፡

## ? መልመጃ፡-"2

፩፡- ከዚህ በታች ባለው ሳጥን ውስጥ ከቀረቡት አያያዥ ቃላት መካከል ለተሰጧችሁ ዓ.ነገሮች ይበልጥ ተስማሚ የሆኑትን በመምረጥ አስገቡ፡፡

1. አልማዝ_________________ታደለች አብረው ገበያ ሄዱ፡፡
2. ዶጎማ ጎበዝ ተማሪ______________ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት ይቀራል፡፡
3. ለወደፊቱ ትልቅ ሰው ትሆናለህ_____________በርትተህ አጥና፡፡
4. አንድ የሚንጠባጠብ የቧንቧ ውሃ________________ያለማቋረጥ የሚፈስ የጉድጓድ ው በጊዜ ርዝማኔ ከፍተኛ የውሃ ብክነት ያመጣል፡፡
5. ክረምት እየመጣ__________________ቤታችንን እናድስ!
6. አርፍጄ ቢሆንም እመጣለሁ__________________አልቀርም፡፡

፪፡- ቀጥለው ከቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ለይታችሁ አሳዩ፡፡

1. ኮሮና ቫይረስ ሰዎችን ለሞት እየዳረገ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡
2. ያቀረበችው የመፍትሔ ሀሳብ ግን ትንሽ ችግር ያለው ይመስለኛል፡፡
3. ማወቅ መለወጥ ነው፤ስለዚህ ለእውቀት እንትጋ!
4. የውበት መለኪያ ውጫዊ ገፅታ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊውንም ይመለከታል፡፡
5. የሰዎችን መብት መንካት ወይም መጣስ አልወድም፡፡

# ክፍለ ትምህርት አርባ ሰባት

## የቃላት ትርጉም

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- ለአዳዲስ ቃላት ልዩ ልዩ ፍች መስጠት ።

## ስልጅ ምክር

“ልጄ ሆይ! ጠላት በዛበኝ፣ምቀኛ አሴረብኝ ብለህ አትጨነቅ። በአለም ላይ የሚኖር ፍጥረት ሁሉ ጠላትና ምቀኛ አለበት። ጠላትና ምቀኛ ያለው ባንተ ላይ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ፡-በፍየል ነብር፣ በበግ ተኩላ፣ በአህያ ጅብ፣ በላም አንበሳ፣ በአይጥ ድመት፣ በዶሮ ጭልፊት…ወዘተ አለባቸው። ሰውም እርስ በርሱ እንዲሁ ነው።

ስለዚህ የሚመጣብህን ነገር ሁሉ በትዕግስት ሆነህ ተቀበለው። በመጨረሻ ግን ሁሉ አላፊ ነውና ጠላቶችህ ያልፋሉ።ወይም አንተ አስቀድመህ ታልፍና ከዚህ አለም መከራና ጭንቀት ታርፋለህ።

ልጄ ሆይ ያለፉትን ሰዎች አስባቸው። እነዚያ ሁሉ ጀግኖች መሬት ገብተዋል፤ እነዚያ ሁሉ አለመኞች፣እነዚያ ሁሉ ቀልደኞችና ፌዘኞች፣እነዚያ ሁሉ ግፈኞች፣እነዚያ ሁሉ በድሃ ላይ የሚስቁና የሚቀልዱ ሁሉ መሬት ገብተዋል፡ ፡ እነዚያ ሁሉ ድሆች ሲበደሉ፣ሲያዝኑ፣ሲያለቅሱ፣ከአንዱ ወደ ሌላው ሀገር ሲሰደዱ፣ሲራቡ፣ሲጠሙ፣ሲታረዙ የነበሩ መሬት ሆነዋል።

የድሃ እንባ ሲፈስ የወንዝ ውኃ የሚፈስ የሚመስላቸው ሰዎች ስንት ነበሩ? ጉልበት አለን ብለው በደካሞች ላይ ያሰቡትን ሁሉ የሚሰሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ሰውን ለማጥፋት እጅግ የሚጥሩ፣ ሰውን ካላጠፉ እንቅልፍ የማይወስዳቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ከዚህ ቀደም የነበሩ ሁሉም መሬት ሆነዋል። ከመሬት የተገኘ መሬት ስለሆነ ወደመሬትም የማይመለስ ሰለሌለ እኛም ነገ እንደዚያው እንሆናለን።

ስለዚህ በማናቸውም ምክንያት ቢሆን የሰው ደስታና ሀዘኑ እጅግ አጭር መሆኑን እንወቅ።”

ምንጭ፡- የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ፣6ኛክፍል፣2004፣85-86

## መልመጃ፡-"፫

ሀ.ቀጥለው በ “ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ትርጉማቸውን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
| --- | --- |
| 1. ያልፋሉ | ሀ.ምስኪን |
| 2. መሬት | ለ.አፈር |
| 3. ድሃ | ሐ.ሲራቆቱ |
| 4. ሲታረዙ | መ.ቀልደኞች |
| 5. ጉልበት | ሠ.ይሞታሉ |
| 6. ምቀኛ | ረ.ሀይል |
| 7. ፍጥረት | ሰ.ተንኮለኛ |
| 8. አሴረብኝ | ሸ.ተፈጣሪ |
| 9. ምክንያት | ቀ.ተመቀኘብኝ |
| 10. ፌዘኞች | በ.ሰበብ |
| | ተ.ምርጫ |

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ፈልጉ፡፡

1. አንተ አስቀድመህ ታልፍና ከዚህ ዓለም መከራና ጭንቀት ታርፋለህ፡፡
2. እነዚያ ሁሉ ጀግኖች መሬት ገብተዋል፡፡
3. ሰውን ለማጥፋት እጅግ የሚጥሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ፡፡
4. ወደ መሬት የማይመለስ ስለሌለ እኛም ነገ እንደዚያው እንሆናለን፡፡
5. በማናቸውም ምክንያት ቢሆን የሰው ደስታውና ሀዘኑ እጅግ አጭር መሆኑን እወቀው፡፡

# ክፍለ ትምህርት አርባ ስምንት

## ቃላት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- የቃል ክፍሎችን መለየትና በዓ.ነገሮች ውስጥ የመጠቀም ሒደት።

## ? መልመጃ:-"4

፩. ቀጥለው በሳጥኑ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በየቃል ምድባቸው በመለያየት አስቀምጡ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰው | ትንንሽ | ዛፍ | ጥቁር | እናት |
| ገደለ | ነብር | በላ | ቤት | አርባ ምንጭ |
| ቀይ | ዲላ | ወፍራም | መሬት | ገላመጠ |
| አንጀት | ልጅ | ቆንጆ | | |

1. ቅጽል:-
2. ስም:-
3. ግስ:-

2.ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት በዓ.ነገር ውስጥ ተጠቀሙባቸው።

ምሳሌ:- አባቴ:-እኔና አባቴ ወደ ሶዶ ልንሄድ ነው።

1. እናት
2. ቅዳሜ
3. ከትናንት ወዲያ
4. ሰማያዊ
5. መጣች

# ምዕራፍ ሰባት

# አርበኞነት

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ስለ አንድ ኢትዮጵያዊ/ት አርበኛ የሕይወት ታሪክ ታዳምጣላችሁ፤
- የራሳችሁን የሕይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፤
- በቡድን በቡድን በመሆን ንግድን የማስመሰል ጨዋታን ትጫወታላችሁ፤
- የቤትና የዱር እንስሳት ስሞችን ትለያላችሁ፤
- ስእሎችን በመመልከት ትናገራላችሁ፤
- በአንብቦ መረዳት ስልት ገላጭ ጽሑፍን ታነባላችሁ፤
- ሐረጋትን በተለያዩ መልኮች ትመሰርታላችሁ፤
- የምሳሌያዊ ንግግሮችን ምንነትና አገልግሎት ትለያላችሁ።

## አስራ ስድስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት አርባ ዘጠኝ

### የሕይወት ታሪክ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የህይወት ታሪክን አዳምጦ መረዳት መቻል።

# የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ

➢ የሕይወት ታሪክ በሁለት መንገዶች ይከፈላል፡፡ ይኸውም፡-

1. የግለሰብ የሕይወት ታሪክና
2. የራስ የሕይወት ታሪክ

1.1. የግለሰብ የሕይወት ታሪክ

1.1.1. የሕይወት ታሪኩ ስለሚጻፍለት(-ላት) ሰው በቂና አሳማኝ መረጃዎች

-የተጻፉ ጽሑፎች ካሉ ማንበብ፤

-ቤተሰቡን በቅርብ ከሚያውቁ ሰዎች መጠየቅ፤

-ቤተ-ዘመዱን በመጠየቅ

1.1.2. የተሰበሰበውን የግለሰብ የሕይወት ታሪክ በቅደም ተከተል ማደራጀት

1.1.2.1. ግለሰቡ የተወለደበትን ቦታ፣ዘመን፣ እንዲሁም ግለሰቡ የሞተ ከሆነ የሞተበትን ዘመን መግለጽ፤

1.1.2.2. ስለአስተዳደጉና የትምህርት ሁኔታ መግለጽ፤

1.1.2.3. ስለፈጸማቸው ተግባሮችና ስላበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ማተት፤

1.1.2.4. ስለ አስደናቂ ስራው ያለንን የግል አስተያየት ማከል፣ ሆኖም አስተያየቱና አመለካከቱ ነጻ ሆኖ እውነት ላይ ይሁን፡፡

1.1.3. ታሪኩን ቀላልና ግልጽ በሆነ ቋንቋ መፃፍ፤

1.1.4. የማስረጃዎቹን ምንጮች በተገቢው ቦታ መግለጽ፡፡

## ? መልመጃ፡-"5

## ፩. ቅድመ ማዳመጥ ተግባራት

1. አርበኝነት ምንድን ነው?
2. "የትነበርሽ ንጉሴ" ማናት? ስለሷ የምታውቁት/የሰማችሁት ነገር ካለ ለመምህራችሁና ለጓደኖቻችሁ ንገሯቸው ከዚያም ቀጣዩን ታሪክ በሚገባ አዳምጡ፡፡

### 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. የትነበርሽ ህፃናትን ለመንከባከብ ከመጡት ሴት መምህራን የተማረችው

ምንድን ነው?

2. የትነበርሽ የህግ ትምህርቷን በማጥናቷ ለአካል ጉዳተኞችና ለችግረኞች ያበረከተቻቸውን አስተዋጽኦዎች ግለፁ፡፡
3. በት/ቤት በልዩ ልዩ ክበባት መሳተፍ ምን ጥቅም ያስገኛል?
4. ያዳመጣችሁት ምንባብ የፈጠረባችሁ ስሜት ምንድን ነው?
5. ባዳመጣችሁት ጽሑፍ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

## ክፍለ ትምህርት ሀምሳ


### የራስ የሕይወት ታሪክ

#### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- ✅ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን ተከትሎ ግለ-ታሪክን ማዘጋጀት፡፡

#### ተግባር-11

የሚከተሉትን መሰረታዊ ሀሳቦች በመጠቀም የየራሳችሁን የሕይወት ታሪክ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡



## ክፍለ ትምህርት ሀምሳ አንድ

### ንግድን የማስመሰል ጨዋታ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- በቢጤ ጨዋታ ላይ በመሳተፍ መናገር መቻል፡፡



### ተግባር-12፡

ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆናችሁ መምህራችሁ የሚሏችሁን መመሪያ በመከተል የእርስ በርስ ጨዋታን አድርጉ፡፡ በመጨረሻም እርስ በርስ አስተያየት ተሰጣጡ፡፡

## አስራ ሰባተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሀምሳ ሁለት


### የእንስሳት ስሞች

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- የእንስሳት ስሞችን ምንነትና አገልግሎት መለየት፡፡

# መልመጃ፡-"6

፩፡-ቀጥለው በክብ ሳጥን ውስጥ የሚሰፍሩ የእንስሳት ስሞች አሉ፡፡ ከጎናችሁ ከተቀመጠ ተማሪ ጋር እርስ በርስ በመወያየት የተለያዩ ስሞችን በሳጥኑ ውስጥ ሙሉ፡፡




፪፡- ከላይ በክብ ሳጥን ውስጥ ካስቀመጣችኋቸው የዱርና የቤት እንስሳት መካከል አንድ አንድ በመምረጥ፡-

1. የእንስሳቱን ስም
2. የእንስሳቱን አይነት(ባህሪ፣መልክ…)
3. የእንስሳቱን አገልግሎት(ካለ) እና
4. የሚገኙበትን ቦታ ግለፁ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ሀምሳ ሶስት

## ስዕልን ተመልክቶ መናገር

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ

- ስዕልን በሚገባ በመመልከት(በመመርመር) ፍሰቱን የጠበቀ ንግግር ማድረግ

## ? መልመጃ:-"7

ጥንድ ጥንድ በመሆን ተከታዩን ስዕል ከመረመራችሁ በኋላ ከስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።



1. በስዕሉ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች ይታዩዋችኋል?
2. በጾታ ምን ያህል ሰዎች አሉ?
3. ስንት ህጻናት አሉ? ምን እየሰሩ ነው?
4. በስዕሉ ላይ የምታዩዋቸው ሴቶች ምን ምን እያከናወኑ ነው?
5. መሬቱ ላይ የተበተነው ምንድን ነው?
6. የሚያዩዋችሁ ቁሳቁሶች/እቃዎች ምን ምንድን ናቸው?
7. በሰዎቹ መካከል ምን አይነት ግንኙነት ወይም ዝምድና ያለ ይመስላችኋል? እንዴት አወቃችሁ?
8. በሥእሉ ውስጥ የትኞቹን ባህሎች ወይም ባህላዊ ጉዳዮች

ተመለከታችሁ? መመልከት የቻላችሁትን በሙሉ ዘርዝሩ።

9. እላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጣችኋቸውን መልሶች መሰረት በማድረግ አንድ ታሪክ ፃፉ።

## ክፍለ ትምህርት ሀምሳ አራት

## ነጭ ሽንኩርት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- በምንባቡ መነሻነት የአንብቦ መረዳት ተግባራትን መከወን።



## መልመጃ፡-"8

### ቅድመ ምንባብ ስራ

1. ከነጭ ሽንኩርት ውጪ ሌሎች የሽንኩርት ዝርያዎች አሉ እንዴ? ካሉ ጥቀሷቸው።
2. ስለ ነጭ ሽንኩርት ጥቅም የምታውቁትን ተናገሩ።

ዛሬ በምድራችን በየአመቱ ሁለት ቢሊዮን ኪሎግራም ነጭ ሽንኩርት ይመረታል፡ ፡ ይህ ሁሉ መጠን በሾርባና በውሃ አማካኝነት የጨጓራ ሲሳይ ብቻ የሚሆን እንዳይመስላችሁ! እንዲያውም በሰለጠነው ዓለም የነጭ ሽንኩርት ተፈላጊነት ከምግብነት ይልቅ ወደ መድሐኒትነቱ ያዘነብላል። በአሁኑ ወቅት የመድሐኒት ኢንዱስትሪዎች ይህችን በየጓሯችን እንደዋዛ የምትበቅለውን ተክል(ነጭ ሽንኩርት)

አፍንጫ አበክሮ እንደሚያነፈንፍ፣ውስጠ ምስጢሩን በገሃድ ይጠቁሙናል፡፡

የነጭ ሽንኩርትን ምስጢር በቅድሚያ በገሃድ ይፋ ያወጣው ሊዊስ ሰተር ነበር፡፡ ሰተር በ1958 ነጭ ሽንኩርት ላይ ባደረገው ፍተሻ የበሽታ ተህዋስያን/ ባክቴሪያ/ በቀጥታ የመግደል ችሎታውን ተገንዝቦ ነበር፡፡ ትኩስ ነጭ ሽንኩርት የደረት፣የጉሮሮ፣የሆድቃና የቆዳ ቁስሎችን/ኢንፌክሽን/ በመፈወስ ረገድ ወደር የለሽ ነው፡፡ ነጭ ሽንኩርት የሆድ እቃን ተግባር በማቀላጠፍ ሰውነታችንን በትርፍነት የሚያካብተውን ጮማ በማቅለጥ፣በእግር ውስጥ የሚበቅሉ ሽታዎችን በመከላከል ጉንፋንንና እንፍሉዌንዛን በማጥፋት በኩልም ድርሻው የላቀ ነው፡፡

ነጭ ሽንኩርት ሲደፈጠጥ አፍንጫን የሚወጋ ሽታ ይወጣዋል፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ፈውሶች ማግኘት ከፈለግን ይህንኑ ከፍተኛ ሽታ ያለውን ፈጭቶ መጠቀሙ የተሻለ መሆኑን ጠቢባን ይጠቁማሉ፡፡

የነጭ ሽንኩርት ክፋቱ ክርፋቱ ነው፡፡ ሆድ ውስጥ ገብቶም መተንፈጉን አይተውም፡ ፡ ወደ አውሮፕላን፣አውቶብሶችና ባቡሮች ገባ ሲባል የነጭ ሽንኩርት መስተንግዶ መጤውን ያስበረግጋል፡፡ ሆኖም ነዋሪው ጉዳዩን ስለሚረዳ እንብዛም አይጨነቅም፡፡ ሞቅ ያለ ግብዣ ላይ ጥሬ ነጭ ሽንኩርትም ከምግብ ጋር አብሮ ይሰለፋል፡፡

እንግዲህ ፈውሱን ከፈለግን ሽታውንም መታገል ግዴታችን ነው፡፡ የነጭ ሽንኩርት ሽታ ከሌላ ሰው አፍ ቢሸተን ጉዳዩን ከጤና አኳያ መመልከት ይኖርብናል፡፡ ሽታው በእጅጉ የሚገንብንና ለሀፍረት የሚዳርገን ከሆነም በእረፍት ቀናት ማለትም ቤታችን በምንውልበት እለት ከአንድና ከሁለት ራስ ያልበለጠ ፈጭተን እንመገብ፡፡

ምንጭ፡- አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ፣6ኛክፍል፣1998፣99

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የተውጣጡ ናቸው፡፡ በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት አገባባዊ ፍች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- አበክሮ፡-አተኩሮ፣አፅንኦት ሰጥቶ

1. ክርፋቱ
2. ፈጭተን
3. ማነፍነፍ
4. ይፋ
5. ተክል
6. ጠቢባን

ለ. ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ።

1. ነጭ ሽንኩርት በዕረፍት ቀን መጠቀሙ ይመረጣል? ለምን?
2. በሰለጠነው ዓለም ነጭ ሽንኩርት በአብዛኛው ለምን አገልግሎት ይውላል?
3. ትኩስ ነጭ ሽንኩርት ከምን ከምን በሽታዎች ይፈውሳል?

# አስራ ስምንተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሃምሳ አምስት

### ሐረግ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የሐረግን ምንነትና አመሰራረት ለይቶ ማስቀመጥ።

### ማስታወሻ

ሆሄያት በስርዓት ተቀናጅተው ትርጉም የሚሰጥ ቃልን ይመሰርታሉ። ቃላት ደግሞ በስርዓት ተቀናጅተው ሐረግን ይመሰርታሉ። ሀረግ እንደ ዓ.ነገር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽን አይዝም።በዚህም ምክንያት አንድን የተሟላ ሀሳብ አይገልፅም። አንድን የተሟላ ሐሳብ ከገለጸ ግን ሀረግ ሳይሆን አረፍተ ነገር ነው።

ምሳሌ፡-

1. የጠዋት ፀሐይ- ይህ ሐረግ ነው።
2. አንገት የደፋው ልጅ- ይህ ሀረግ ነው።
3. የልጆች ጨዋታ- ይህም ሐረግ ነው።
4. ልጆች ተጫወቱ- ይሄ ዓ.ነገር ነው።
5. አንገቱን ደፋ- ይሄም ዓ.ነገር ነው።

# መልመጃ:-"9

ሀ. በምሳሌው መሰረት በምድብ "ሀ" ሥር ለቀረቡት ቃላት ከምድብ "ለ" ስር ተስማሚያቸውን በመምረጥ ሐረግ መስርቱና በምድብ "ሐ" ስር ጻፉ::

| "ሀ" | "ለ" | "ሐ" |
|---|---|---|
| 1. ምሳሌ:-የፅዳት | ሰራተኛ | የፅዳት ዘመቻ |
| 2. ትኩስ | እንጀራ | ______________ |
| 3. ትጉህ | መካከል | ______________ |
| 4. ፍም | ዘመቻ | ______________ |
| 5. ውድ | እሳት | ______________ |
| 6. ፈጣን | ብርጭቆ | ______________ |
| 7. ትልቅ | ዋጋ | ______________ |
| 8. ጎጂ | ባህል | ______________ |
| 9. ብጣሽ | አክባሪ | ______________ |
| 10. የጉልበት | ሎተሪ | ______________ |
| | ወረቀት | ______________ |

ለ. በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ሐረግ መስርቱ::

ምሳሌ:- ጥቁር- 1. ጥቁር እንግዳ

2. ጥቁር ልብስ

ሀ. ቀጣይ

ለ. ሯጭ

ሐ. ብልህ

መ.ደብዛዛ

ሠ.ዘርዛራ

ረ.ደማቅ

# ክፍለ ትምህርት ሃምሳ ስድስት

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- የምሳሌያዊ ንግግሮችን አገልግሎት መለየት፡፡

### ማስታወሻ:

ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚታዩትን አስነዋሪ ባህርያት ለመዋጋት፤ መልካም ስነ-ምግባር እንዲዳብር፤ፍቅር፣ታማኝነት፣ደግነት፣ትህትና፣እውነት፣ሰላም እንዲሰፍን፣ትዕግስት እንዲኖር የሚያሳስቡና የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ምሳሌያዊ አነጋጋሮች/አባባሎች የማስተማር፣ የመግታትና መቆጣጠር፣እፎይታን የማስገኘት፣የማስተማር እንዲሁም የመትከልና ማጠናከር አገልግሎት አሏቸው፡፡

### ተግባር-13

፩.ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ የሚነገሩትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰብስባችሁ በማምጣት ትርጉማቸውን በክፍል ውስጥ በመወያየት አቅርቡ፡፡

2.ቀጥለው የቀረቡትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ትርጉማቸውን ፈልጉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ.ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፡፡ (ጥሩ ስራ ሁሌም ሲታወስ/ሲወደስ ይኖራል፡፡)

ለ. ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ (የማይጨበጥ ምኞት፣ተስፋ)

1. የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ፡፡
2. ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል፡፡
3. ልጅ ቢያባብሉት ያለቅሳል፡፡
4. አባት ያበጀው ለልጅ በጀው፡፡
5. ደፋርና ጪስ መውጫ አያጣም፡፡
6. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

# ምዕራፍ ስምንት

# ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- ልዩ ልዩ የአነባበብ ብልሀቶችን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፤
- ቃላት በገቡበት አውድ የተለያየ ፍች እንዳላቸው ታብራራላችሁ፤
- የእንቶቅልሽ አቀራረብ መመሪያን ተከትላችሁ ልዩ ልዩ እንቆቅልሾችን ትናገራላችሁ፤
- የተቀረፀ ታሪክን ታዳምጡና የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን ታከናውናላችሁ፤
- ለቃላት ልዩ ልዩ ትርጉሞችን ትሰጣላችሁ፤ይዘቶችንም ታብራራላችሁ፤
- የሐረግ ምስረታ ታደርጋላችሁ፤
- የዕለት ውሏችሁን ትጽፋላችሁ::

## አስራ ስምተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሃምሳ ሰባት


### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎቻችን



**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የአነባበብ ብልሃቶችን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መመለስ መቻል::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ባህላዊ ሙዚቃ ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስም ዘርዝሯቸው?

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ ስለሆነች የተለያዩ ባህሎች በውስጧ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ባህሎች የየራሳቸው መገለጫ አላቸው፡፡ ከነዚህ መገለጫዎች መካካል ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ባህላዊ ሙዚቃ ከጥንት ጀምሮ የደስታና የሐዘን መግለጫ በመሆን ለብሄር ብሄረሰቦች እያገለገለ ይገኛል፡፡

ሙዚቃ ምንም እንኳን ከአንደበት በዜማ መልክ ቢፈልቅም ያለ አጃቢ የሙዚቃ መሳሪያዎች አይደምቅም፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያም ብዙ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሏት፡፡ እነዚህ ባህላዊ መሳሪያዎችም የትንፋሽ፣የምት እና የክር በመባል በሶስት ይከፈላሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚገኙት ባህላዊ የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል

ዋሽንት፣እምቢልታ፣መለከት፣ድንኬ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት ደግሞ ከበሮ፣ነጋሪት፣አታሞ ወዘተ ሲሆኑ፣ የክር የሙዚቃ መሳሪያ ከሚባሉት ደግሞ ክራር፣ማስንቆ፣በገና ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ፡-ለሰርግ ዘፈኖች፣ ለሀዘን(ለለቅሶ)፣ለበዓል ዘፈኖች፣ለሀይማኖታዊ አገልግሎት፣ለስራ ማከናወኛ (ለአረም፣ለአጨዳ…)፣ለቀረርቶ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ ቢውሉም ሌሎች ያልተጠቀሱ እንዳሉ ሊታወቅ ይገባል፡፡

## ? መልመጃ፡-፫

ሀ. ተከታዮቹን ከምንባቡ የተገኙ ቃላትን አውዳዊ ፍች በቃል ተናገሩ፡፡

1. መኖሪያ
2. ተጠቃሽ
3. መፍለቅ
4. ትንፋሽ
5. ክር
6. ጋብቻ
7. መገለጫ
8. አንደበት
9. አጃቢ
10. ብሔረሰብ

ለ. በ“ሀ” ረድፍ ያሉትን መሰረተ ሐሳቦች በ“ለ” ረድፍ ካሉት ተመሳሳያቸው ጋር በጽሑፍ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
| --- | --- |
| 1. የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ሀ.ክራር፣ማስንቆ፣በገና፣ ወዘተ |
| 2. የትንፋሽ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ለ.ለስራ ማከናወኛ(ለአረም፣ለአጨዳ) |
| 3. የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች | ሐ.ከበሮ፣ነጋሪት፣አታሞ፣ወዘተ |
| 4. የማህበራዊ፣ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | መ.ለሽለላ፣ለፉከራ፣ለቀረርቶ |
| 5. የኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች | ሠ.ለጋብቻ፣ለሰርግ፣ለሀዘን፣ለበዓል |
| | ረ.ዋሽንት፣እምቢልታ፣መለከት፣ድንኬ |

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የትንፋሽ መሳሪያ የሆነው--------------ነው፡፡

ሀ.ክራር ለ.ከበሮ ሐ.ዋሽንት መ.አታሞ

2. ከሚከተሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ የምት መሳሪያ ያልሆነው-----ነው፡፡

ሀ.ከበሮ ለ.ነጋሪት ሐ.ዋሽንት መ.አታሞ

3. የክር የሙዚቃ መሳሪያዎች ከሚባሉት መካከል የሚመደበው የትኛው ነው?

ሀ.ክራር ለ.ማስንቆ ሐ.በገና መ.ሁሉም መልስ ነው

# አስራ ዘጠነኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሃምሳ ስምንት

### የቃላት ትርጉም

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የቃላትን አውዳዊ/አገባባዊ ፍች መለየት፡፡

- የቃላት አገባባዊ ትርጉም፡- አንድ ቃል በተለያዩ ዓ.ነገሮች ውስጥ ሲገባ የተለያዩ ትርጉሞችን የሚሰጥበት ሒደት ነው፡፡ ምሳሌ፡-
- ልጁ የከተማው ዋና አስተዳዳሪ ነው/መሪ/፡፡
- -ተመስገን ዋና በጣም ይወዳል፡፡(መዋኘት)
- ሰዎቹ በአንድ አፍ ተስማሙ፡፡(በሙሉ ድምጽ አፀደቁ)
- -ልጅቱ አንድ አፍ ነች፡፡(ገና ትንሽ ነች)
- -ወ/ሮ ጫኪሴ ጥሩ ጠላ ጠመቁ፡፡/የመጠጥ አይነት/
- -ልጁ ትምህርት ጠላ፡፡ /አልወደደም/

## ? መልመጃ፡-#፩

፩. በሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት በአገባባቸው መሰረት ፍችያቸውን ስጡ፡፡

1. አጪሶ ጥሩ መጽሐፍ ደረሰ፡፡
2. ሚጁ ልክ በቀጠሮው ሰዓት ደረሰ፡፡
3. መሬቱን ሊያርሱ በሬ ጠምደዋል፡፡
4. ጨርቃቸውን በውኃ ሊያርሱ ነው፡፡
5. ወርቃለማሁ ስዕሉን በደንብ ሳለ፡፡
6. ሰውየው ጉንፋን ይዞት በሀይል ሳለ፡፡
7. ሌቦቹ በፖሊስ ታድነው ተያዙ፡፡
8. ካጋጠመው አደጋ ታድነው ዘንድ ለመናት፡፡
9. ጧትና ማታ መጨቃጨቁ እጅ እጅ አለኝ፡፡
10. ምግቡ በመቆየቱ እጅ እጅ አለ፡፡

2.የሚከተሉትን ሐረጎች በተለያዩ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ትርጉሞች እንዲሰጡ አድርጋችሁ ፃፏቸው፡፡

ሀ. ሆዴን አለ ለ.ጥርሱን ነከሰ ሐ. ሆዱን በላው መ. እጅ ሰጠ

ሠ. አንጀት በላ

## ክፍለ ትምህርት ሃምሳ ዘጠኝ

# እንቆቅልሽ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- የእንቆቅልሽ አቀራረብ መመሪያን ተከትሎ እንቆቅልሾችን ማቅረብ ወይም መናገር መቻል፡፡

እንቆቅልሽ፡-በጠያቂና ተጠያቂ መካከል የሚደረግ የልጆችን አዕምሮ ለማስላት፣ አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ የአስተሳሰባቸውን አድማስ ለማስፋት፣ የሰውን፣የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪና ቅርጽ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዳ የውድድር መንፈስ የሚታይበት የጥያቄና መልስ ስነ-ቃል ነው፡፡ ምንጭ፡ -የስነ-ጽሑፍ መሰረታውያን፣ዘሪሁን አስፋው፣2004፣38-40

## ተግባር-14

ሀ. ተማሪዎች! ቀደም ሲል በራሳችሁ የምታውቁትንና እንደዚሁም ከወላጆቻችሁና ከአካባቢያችሁ ሰብስባችሁ በማምጣት በክፍል ውስጥ ተራ በተራ እንቆቅልሾችን ተጠያየቁ፡፡

ለ. የሚከተሉትን እንቆቅልሾች ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ እያነበባችሁ (እየተጠያየቃችሁ) መልእክታቸውን ግለጹ፡፡

**ጥያቄ** **ፍች**

1. ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ______________________________
2. ቀይ ዘንዶ እዋሻ ውስጥ ተጋድሞ__________________________
3. ከአባቷ ትበልጣለች ከእናቷ ታንሳለች _______________________
4. ሲቀመጥ ረጅም ሲቆም አጭር____________________________
5. ሺ ዓይን አለው አጥንት የለው____________________________
6. ትንሽ ማረሻ አፈር ሳይነካት ታርሳለች______________________
7. ሲሄድ ቢውል የማይደክመው_____________________________
8. እናቷ ጥቁር ልጆቿ ነጫጭ______________________________

# ክፍለ ትምህርት ስልሳ

## ወንድማማቾቹ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- "ወንድማማቾቹ" የሚለውን ታሪክ(ትረካ) በሚገባ ማዳመጥና የአዳምጦ መረዳት ተግባራትን መፈፀም።

## ? መልመጃ፡-#2

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች ካዳመጣችሁት ታሪክ የተውጣጡ ናቸው። እንደአጠያየቃቸውም ምላሽ ስጡ።

1. የሁለቱ ወንድማማቾች መተዳዳሪያቸው ምንድን ነው?
2. ላጤውና ባለትዳሩ በየግላቸው ምን ምን ተግባራትን አደረጉ?
3. ሁለቱ ወንድማማቾች በመጨረሻ ምን አጋጥሟቸዋል?

ለ. ቀጥለው የቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ካዳመጣችሁት ትረካ የተወሰዱ ናቸው። በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡትም ከ"ለ" ክፍል በሀሳብ የሚዛመዳቸውን በመለየት አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አደላድያለሁ | ሀ.መውለድ፣መፍጠር |
| 2. እየባረከልኝ | ለ.እያበረከተልኝ |
| 3. ማፍራት | ሐ.ባገኙት |
| 4. ላጤው | መ.የሚኖሩት |
| 5. ባለ ፀጋ | ሠ.አመቻችቻለሁ |
| 6. በወረሱት | ረ.ያላገባው |
| 7. የሚተዳደሩት | ሰ.ሀብታም |
| | ሸ.እየፈወሰኝ |

# ሃያኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ አንድ

### የቃላት ትርጉም

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ ዓላማ**

- ለልዩ ልዩ ቃላት ትርጉሞችን መስጠትና ይዘቶችን ማብራራት።

## የቤት ውስጥ ጥንቃቄ

የቤት ውስጥ ጥንቃቄ ምንድን ነው? የቤት ውስጥ ጥንቃቄ በቤት ውስጥ የሚከናወኑ የተለያዩ ክንውኖችን ለሰው ልጅ ኑሮ አመቺ ማድረግ ማለት ነው። በቤት ውስጥ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ የሚከሰቱ አደጋዎች፣በሽታዎች የመሳሰሉትን ለመከላከል የሚደረጉ የተለያዩ ጥንቃቄዎችን ያካትታል። ከጥንቃቄዎቹም ውስጥ ለእንስሳት፣ለተባይ ማጥፊያና ለፈዋሽ መድሐኒቶች፣ ስለት ላላቸው ነገሮች ወዘተ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። ከእንጨት ወይም ከተለያዩ ተቀጣጣይ ነገሮች የሚገኝ እሳት፣ ለተለያዩ የቤት ውስጥ ስራዎች እንደሚጠቅም ይታወቃል። ይሁን እንጂ በተገቢው መንገድና ጥንቃቄ ተጠቅመን በወቅቱ ካላጠፋነው ከፍተኛ የሆነ የሕይወትና የንብረት ጥፋትን ያስከትላል። ስለዚህ እሳትን ተጠቅመን ስንጨርስ ሳንዘናጋ በአግባቡ ማጥፋት ይኖርብናል።

የተባይ ማጥፊያና ፈዋሽ መድሀኒቶች በአይነታቸው እጅግ በርካታ ናቸው። ለምሳሌ፡- በፈሳሽ፣በዱቄት፣በጠጣር፣ወዘተ መልክ የሚዘጋጁ አሉ። የተባይ ማጥፊያ መድሐኒት ጎጂ የሆኑ ነፍሳትን፣ተባዮችንና የመሳሰሉትን ለማጥፋት ጠቃሚ ነው። ፈዋሽ መድሐኒት በሐኪም ትዕዛዝ ሲወሰድ ለሰው ልጅ ጠቃሚ ነው። ነገር ግን መድሐኒቶች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ውለው ህፃናት በማይደርሱበት ቦታ ካልተቀመጡ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ሊያመዝን ይችላል።

እንደ ቢላዋ፣ማጭድ፣ምላጭ የመሳሰሉትን ስለት ያላቸውን ቁሳቁሶች ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እናውላቸዋለን። እንደ መርፌ፣ወስፌ፣ወዘተ ያሉ ሹል ነገሮችንም ለተለያዩ የቤት ውስጥ ስራዎች እንጠቀምባቸዋለን። ይሁን እንጂ በጥንቃቄ ካልተጠቀምንባቸውና ሕፃናት በማይደርሱበት ቦታ ካላኖርናቸው ጉዳታቸው የከፋ

ይሆናል። ስለዚህ በአገልግሎት ላይም ሆነ ከአገልግሎት በኋላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

በአጠቃላይ የቤት ውስጥ ጥንቃቄ ሲባል እሳት አያይዞ አለመርሳት፣የተባይ ማጥፊያና ፈዋሽ መድሐኒቶችን በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ፣ስለት ያላቸውን ነገሮች ከሕጻናት ማራቅ ወዘተ የመሳሰሉትን ይመለከታል።

ምንጭ፡- አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፣5ኛክፍል፣2008፣22

## ? መልመጃ፡-#፫

፩. ከዚህ በታች ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ለእያንዳንዱ በፍች ተመሳሳያቸውን መርጣችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡- ያስፈልጋል፡- ሀ.ያሻል ለ.ይገባል ሐ.ይኖራል መ.መልስ የለም
የዚህ ጥያቄ መልስ“ሀ”ነው።

1. ማቀጣጠል፡ ሀ.ማነጋገር ለ.ማያያዝ ሐ.ማሰለፍ
2. ማዘጋጀት፡ ሀ.ማሰባሰብ ለ.ማሰናዳት ሐ.መብላት
3. መጠበቅ፡ ሀ.መስራት ለ.ማገናዘብ ሐ.ማገድ
4. ባሕርይ፡ ሀ.ዕውቀት ለ.ጠባይ ሐ.ህልም
5. መዛመት፡ ሀ.መዳረስ ለ.መጓዝ ሐ.መምጣት
6. መሻት፡ ሀ.መፈለግ ለ.ማጣት ሐ.ማግኘት
7. ክትትል፡ ሀ.ንፅፅር ለ.ድርድር ሐ.ቁጥጥር

2.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብተራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለተሰመረባቸው ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢውን አገባባዊ ፍች መርጣችሁ መልሱ።

1. እሳት <u>አቀጣጥሎ</u> አለመስራት

   ሀ.አያይዞ ለ.አጣልቶ ሐ.ሰባብሮ መ.አዳፍኖ

2. ስለት ያላቸው ነገሮች ከህፃናት ማራቅ ከአደጋ <u>ያድናል</u>።

   ሀ.ይጥላል ለ.ያጋልጣል ሐ.ይፈውሳል መ.ይከላከላል

3. ምግብን በጥንቃቄ <u>በማዘጋጀት</u> እና በመሸፈን ንፅህናውን መጠበቅ ይቻላል።

   ሀ.በመፍጨት ለ.በመሰብሰብ ሐ.በማሰናዳት መ.በመብላት

4. የመጠጥ ውኃ ንፁህ ካልሆነ ለተለያዩ ውሃ ወለድ በሽታዎች ልንጋለጥ እንችላለን።

ሀ.ከውሃ ለሚመጡ ለ.ብክለት ሐ.የተመረዙ መ.የጉድጓድ ውኃ

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ ሁለት

## የስማዊ ሐረግ ምስረታ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- በቃላት አማካይነት ልዩ ልዩ ስማዊ ሐረጎችን መመስረት።

## ? መልመጃ:-#4

፩.ቀጥለው በቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ የትኞቹ ስማዊ ሐረግ እንደሆኑ በመለየት አስቀምጡ።

ምሳሌ:- -ለመስቀል የገዛነው በሬ ዛሬ ጠፋ።(የገዛነው በሬ)
-የመስቀሌ መኪና ተሳቢ ነው።(የመስቀሌ መኪና)

1. ሰውን ሰው ያሰኘው ስራና ስራው ነው። (          )
2. አንጅሎ ቁልቁለቱ ላይ እንደደረሰ ተንሸራቶ ወደቀ። (          )
3. እጅግ የተዋበችዋ ጨረቃ ዛሬ አልወጣችም። (          )
4. በዘመን መለዋወጫ ትምህርት አይከፈትም። (          )
5. ማርቆስ መጽሐፉን በፍጥነት አንብቦ ጨረሰ። (          )

2.ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት ስሩ።

ምሳሌ:- -ታታሪ ገበሬ = ዘበርጋ ታታሪ ገበሬ ነው።
-የቆዳ ጫማ = አባቴ ለትምህርት ቤት የቆዳ ጫማ ገዛልኝ።

1. የይርጋ ጨፌ ቡና
2. የምወዳት ልጅ
3. ትልቁ በሬ
4. የእኛ ፈረስ
5. ቆንጆው ልጅ
6. የአርባ ምንጭ ውሃ

# ክፍለ ትምህርት ስልሳ ሶስት

## የዕለት ውሎ ማስታወሻ

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- የማስታወሻ አያያዝ ዘዴን ተጠቅሞ የቀን ውሎን ማዘጋጀት

## ተግባር-15

ከታች የቀረበውን የዕለት ውሎ አጻጻፍ ቅርፅን ተከትላችሁ መምህራችሁ በሚሏችሁ መሰረት የቀን ውሏችሁን በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው፡፡

ምሳሌ፡-

አንድ ቀን በጣም ማልጄ ተነሳሁ፡፡ ብዙም ጤንነት አልተሰማኝም ነበር ሆኖም እንደነገሩ ለባበስኩና ወደ መጸዳጃ ቤት አዘገምኩኝ፡፡ ትንሽ እየተንገዳገድኩኝ ስሄድ ልጆች ሲጫወቱ በመንገድ ያስቀመጡት ድንጋይ አደናቀፈኝና ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ፡፡ እንደምንም ታግዬ ደርሼ ተመለስኩና ተጣጥቤ ብዙም ሳይጥመኝ ቁርሴን ቀማመስኩና ወደ እለት ተግባሬ ተሰማራሁ፡፡

ወደ ስራ ቦታዬ ጥቂት አርፍጄ እንደደረስኩኝ ተንኮለኛው የቅርብ አለቃዬ እሳት ጎርሶ ጠበቀኝ፡፡ ለምን እንዳረፈድኩ ሲጠይቀኝ የገጠመኝን እክል ብነግረውም እንኳ ሊሰማኝ አልፈለገም፤ይባስ ብሎ ሊያጠቃኝ አሴረብኝ፡፡ እኔም የማደርገውን ባጣ ለካስ ለዚህ ነበር እንዴ ያመመኝ? ብዬ ዝም አልኩ፡፡

ከመምህር በቀለ ሙዳ(ዲመትከ)

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ስሁና ስኬት

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች:ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- የዝምታ የንባብ ዘዴን ተጠቅማችሁ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን ትሰራላችሁ፤
- ሐሳባችሁን በነፃነትና በፍጥነት በማመንጨት ውይይት ታካሂዳላችሁ፤
- የተለያዩ እፅዋትን ስምና አገልግሎት ትለያላችሁ፤
- የጥምር ቃላትን ምስረታ ታዳምጣላችሁ፤
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ስሞችንና ግሶችን ትለያላችሁ፤
- የሠላምታ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፤
- የፈሊጣዊ ንግግሮችን ምንነትና ትርጉም ትለያላችሁ፤

## ሃያ አንደኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ አራት

### የአውራ አምባ ማሕበረሰብ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የዝምታ አነባበብ ስልትን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ስራን መስራት፡፡





የአውራ አምባ ማህበረሰብ ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ በሆኑ የአማራ ብሔር አባላት ከ1964 ዓ.ም ወዲህ የተመሰረተ አነስተኛ ማህበረሰብ ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት የየትኛውም ሐይማኖት ተከታይ አይደሉም፡፡ በመኖሪያ ስፍራቸው፣ በአካባቢያቸው ከሚገኙ የአማራ ህዝብ በተለየ ሁኔታ ቤተክርስትያን፣መስጊድ ወይም ሌላ ዓይነት የአምልኮ ስፍራ የላቸውም፡፡ የሕይወት ፍልስፍናቸውና እምነታቸው ስራ መሆኑን፤ይህም የሕይወት አተያይ በስራ ባህላቸው ያመጡት የባህርይ ለውጥ መሆኑን የማህበረሰቡ መስራች መሪ አቶ ዙምራ ይመሰክራሉ፡፡

የአውራ አምባ ማህበረሰብ አባላት በጾታ ላይ የተመሰረተ የስራ ክፍፍል ባህል አይከተሉም፡፡ ከሌሎች ማህበረሰቦች በተለየ መንገድ የሴቶች ስራ ተደርገው የሚታዩትን እንጀራ የመጋገር፣ወጥ የመስራት፣ጥጥ የመፍተል ወዘተ የመሳሰሉ የማጀት ሥራዎችን ወንዶች ያከናውናሉ፡፡ ሴቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ምንም ባህላዊ ተጽዕኖ ሳያግዳቸው በሬ ጠምደው ያርሳሉ፣የሽመና ስራ ላይ ይሰራሉ፡፡ በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የሚከበር የበዓል ቀን የለም፡፡ የአመቱ ቀናት በሙሉ የስራ ቀኖች ናቸው፡፡

የጋብቻ ባህላቸውም ከሌላው ማሕበረሰብ የተለየ ነው፡፡ የማህበረሰቡ ደንብ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች እንዲያገቡ አይፈቀድም፡፡ጋብቻ ቤተሰብ ለመመስረት በደረሱ የማህበረሰቡ አባላት የሚፈፀም ሆኖ በተጋቢዎች ምርጫ ብቻ ይከናወናል፡፡ ወላጆች የልጆቻቸውን የጋብቻ ምርጫ በመወሰን ረገድ ምንም ሚና የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ለጋብቻ የሚያስፈልገው ወጪ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለሰርግ የሚባክን ጊዜና ሀብት የለም፡፡ ጋብቻውን በራሳቸው ሥርዓት በሶስት ሽማግሌዎች ይፈጽማሉ፡፡ግብዣ ብሎ ነገር የለም፡፡ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ፈጽመው ወደ ስራ ይሰማራሉ፡፡

በሞት የተለየ የማህበረሰቡ አባል በሶስት ወይም በአራት ሰዎች ይቀበራል፡፡

ለሀዘን ብሎ የሚወጣ ወጭና የሚባክን ጊዜ የለም። አቅመ ደካሞችን በጋራ መርዳት የማሕበረሰቡ የጋራ ኃላፊነት ነው።የተለየ የአመጋገብ ባህል የላቸውም፤ የጾም ቀን ወይም ለአንድ አልያም ለተወሰኑ ቀኖች የማይመገቡት የምግብ አይነትም የለም።

በአጠቃላይ የማህበረሰቡ አባላት እምነትና ባህል በአካባቢያቸው በሚገኙ የአማራ ብሔር አባላት ዘንድ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አለው ለማለት አያስደፍርም። ዳሩ ግን በማሕበረሰቡ ላይ የሚደርስ ተፅዕኖ የለም። ማህበረሰቡ የራሱን ፍላጎትና እምነት በነጻነት ለማራመድ ችሏል። ከጊዜ ወደጊዜም የማህበረሰቡን የኑሮ ዘይቤ የሚደግፉ፣ የስራ ፍልስፍናቸውን የሚያበረታቱ የአማራና የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች አባላት ቁጥር እያደገ መጥቷል። ማሕበረሰቡም ለአማራ ህዝብ ሕብረ ባህላዊነትና የመቻቻል ባህል ማሳያ ወይም ተምሳሌት ለመሆን በቅቷል።

ምንጭ፡- ጌታቸው በለጠ፣የጥበባት ጉባኤ፣2004፣11-13

## ? መልመጃ፡-#5

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባነበባችሁት መሰረት በጽሑፍ ምላሽ ስጡ።**

1. የአውራ አምባ ማህበረሰብ የት ይገኛል?
2. የአውራ አምባ ማሕበረሰብ የሥራ ባህል ከሌሎች ማህበረሰቦች በምን መልኩ እንደሚለይ ግለፁ።
3. የማሕበረሰቡ የጋራ ሀላፊነቶች የሆኑትን ዘርዝሩ።

**ለ. ቀጥለው በ“ሀ” ረድፍ ለቀረቡት ቃላት በፍች ተመሳሳይ የሆኑትን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሐይማኖት | ሀ.ይፈጸማል |
| 2. አካለ መጠን | ለ.የሚጠፉ |
| 3. ይከናወናል | ሐ.እምነት |
| 4. የሚባክን | መ.ለጥቂት |
| 5. ለተወሰኑ | ሠ.ለጋብቻ መድረስ |
| 6. አያስደፍርም | ረ.ተምሳሌት |
| 7. ማሕበረሰብ | ሰ.የሚረዱ |
| 8. መፍተል | ሸ.አያስችልም |
| 9. የሚደግፉ | ቀ.ማባዘት |
| 10. ማሳያ | በ.ብሔረሰብ |
| | ተ.ዘመድ |

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ አምስት

### ውይይት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- ሀሳብን በፍጥነትና በነጻነት በማመንጨት ውይይት ማካሄድ።

### ተግባር-16

በቡድን በቡድን በመሆን ቀጥለው ከቀረቡላችሁ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ውይይት አካሂዱ።

1. የውኃ ብክለትንና ብክነትን እንዴት መከላከል/መቀነስ ይቻላል?
2. ሥራ አጥነትን መቅረፍ የሚቻለው እንዴት ነው?
3. በረሃማነት እንዳይስፋፋ ምን ማድረግ አለብን?
4. ኩረጃን እንዴት መከላከልና ማስወገድ ይቻላል?

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ ስድስት

### የዕጸዋት ስሞች

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- ልዩ ልዩ የዕጸዋትን ስምና አገልግሎት መለየት መቻል።











# ? መልመጃ:-#6

## ሀ.ስዕሉን ተመልክታችሁ ተናገሩ፡፡

1. ከላይ በቀረበው ምስል ውስጥ ምን ምን ዕጸዋት ይገኛሉ?
2. የዕጸዋቶቹ ጥቅምስ ምንድን ነው?

## ለ.ከታች በቀረበው ባዶ ሳጥን ውስጥ ሀገር በቀልና መጤ (የውጭ ሀገር) ዕጸዋትን በመለየት ሙሉ፡፡



# ሃያ ሁለተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ ሰባት

### የጥምር ቃላት ምስረታ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- ጥምር ቃላትን በማዳመጥ መጻፍና መጥራት፡፡

### ተግባር-17

ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያስደምጧችሁን ጥምር ቃላት በትክክል በማዳመጥ በደብተራችሁ ጻፏቸውና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ ስምንት

### ስሞችንና ግሶችን መለየት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- በዓ.ነገር ውስጥ ስሞችንና ግሶችን መለየት፡፡

### ? መልመጃ፡-#7

ሀ.ቀጥለው በዓ.ነገሮቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ስምና ግስ መሆናቸውን ለዩ፡፡

ምሳሌ፡- የክፍላችን ተማሪዎች ፀባየ ሰናዮች ናቸው፡፡(ስም)

1. የአማርኛ መምህራችን ዛሬ ትመጣለች፡፡
2. የመስቀል ወፏን ተመለከትኳት፡፡
3. ሐሳብህን እንደመጣልህ አትናገር፡፡
4. የአሜሪካኗ ላም ሁለት ጊዜ ወልዳለች፡፡
5. መጽሐፉን በተገቢው ቦታ አስቀምጠው፡፡

ለ.ከዚህ በታች በሳጥን ውስጥ ያሉት የትኞቹ ስሞች፣የተኞቹ ደግሞ ግሶች እንደሆኑ ለይታችሁ በሰንጠረዥ አስቀምጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| -በላ | -ሰው | -መድሐኒት | -ደነፋ |
| -ተማሪዎች | -ገፋች | -ወራቤ | -አንኮራፋ |
| -አንበሳ | -ሰቀለ | -ወልቂጤ | -ዳገት |
| -ፀሐይ | -ቀማ | -ሄደ | -አልማዝ |

## ክፍለ ትምህርት ስልሳ ዘጠኝ

### የሠላምታ ደብዳቤ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የሰላምታ ደብዳቤ ማዘጋጀት።

## ተግባር፦18

ቀጥሎ የቀረበውን አስረጂ/ምሳሌ መሰረት አድርጋችሁ አንድ የሰላምታ ደብዳቤ ለወዳጆቻችሁ/ለዘመዶቻችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

በቦታ ርቀት ሳቢያ አካል ለአካል ተገናኝተው ሀሳባቸውን መለዋወጥ ያልቻሉ ዝምድና ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው ሰዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ በማስፈር በገጽ ለገጽ ወይም በድረ ገጽ የሚያደርጉት የግንኙነት መፍጠሪያ መንገድ ደብዳቤ ተብሎ ይጠራል።በደብዳቤም ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ይነሳሉ።

ቀን-24/08/2014 ዓ.ም
ተማሪ አዲሴ አጪሶ
አዲሎ 1ኛደረጃ ት/ቤት
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 521
አዲሎ

ለ፡-ብርቱካን ተመስገን

አርባምንጭ፣

ይድርስ በጣም ለምወድሽና ለማከብርሽ ውዷ እናቴ አማ እንደምን ነሽ? እኔና አባቴ ካንቺ ሀሳብና ናፍቆት በስተቀር ደህና ነን፡፡ አንቺ ከሄድሽ ጀምሮ ቤቱ ጭር ብሏል፤ ሰው ያለበትም አይመስልም፡፡ ስራሽን ጨርሰሽ እስከምትመጪ ናፍቆትሽን አልቻልኩም፡፡

ይኸውልሽ በቀደም አባቴ ሊያዝናናኝ ወሰደኝ፡፡ ነገር ግን ምንም ሳልደሰትለት መጣን፡፡ ያላንቺ ሁሉም አያምርም፡፡ አደራ ስላልሽኝ ግን ትምህርቴ ላይ እየጎበዝኩ ነው፡፡ በመጀመሪያው “ሴሚስተር” አንደኛ ወጥቼልሻለሁ፡፡ ስልክ ከሰራልሽ ደዋውይልን፤አደራሽን እናቴ፡፡

በተረፈ በሰላም እንዲያገናኘን ፈጣሪዬን እለምነዋለሁ፡፡ አባቴም በጣም ነው የሚወድሽ! ቶሎ ነይለን፡፡እንወድሻለን አማዬ፡፡

ቻው! ቻው! ቻው!

ውዱ ልጅሽ ነኝ!!

## ክፍለ ትምህርት ሰባ

# ፈሊጣዊ አነጋገሮች

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- የፈሊጣዊ ንግግሮችን ምንነትና ትርጉም መለየት፡፡

የፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች፡- ፈሊጣዊ አነጋገሮች በመዝገበ ቃላት ውስጥ ከሚታወቁት የቃላት ፍችዎች እጅግ በበለጠ መልዕክትን ያስተላልፋሉ፡፡ አንባቢውም ሆነ አድማጩ የሚተላለፈውን መልእክት በጉልህ ይመለከተዋል፤ይሰማዋል፡፡

ምሳሌ፡-

1. ውሽቱ ስለታወቀበት ሀፍረት ለበሰ =/አፈረ/
2. እንደተለመደው መሬት ልሶ ነው የተሸለመው=/ተለማምጦ/
3. ትናንት ማታ ገንዘብ ስበትን አመሸሁ=/በከንቱ ሳጠፋ/

## ? መልመጃ፡-#8

፩፡- በሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ያሉትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለይታችሁ በማውጣት ትርጉም ስጡ፡፡

ሀ.እንቅልፍ አታለለኝና ካልጋዬ ሳልነሳ ጎህ ቀደደ፡፡
ለ.በአዲስ አበባ ከተማ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች እየበዙ ነው፡፡
ሐ.ሰውየው አፈ ቅቤ ነው፡፡
መ.ሲዳማና ደቡብ ክልል ኩታ ገጠም ናቸው፡፡
ሠ.ሁሉ አማረሽ በመሆኗ አንዱንም ሳታሳካ ቀረች፡፡

2፡- በሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ዓረፍተ-ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- እግሬ አውጪኝ፡- ሌባው ስለተነቃበት እግሬ አውጪኝ አለ፡፡

1. ሐሞተ ቢስ
2. ሆደ ሰፊ
3. የውኃ ሽታ ሆነ
4. ነጋ ጠባ
5. ስመ ጥሩ

# ምዕራፍ አስር

# አጭር ልቦለድ

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች:ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ከልቦለዱ ውስጥ ዋና ዋና ገጸባህርያትን(ዋና ዋና የታሪኩ ባላቤቶችን) እና መቼቶችን(ድርጊት የሚፈፀምባቸውን ጊዜና ቦታ)ትለያላችሁ፤
- የድርሰትን ምንነት፣አጻጻፍ ስልትና አይነቶችን ትለያላችሁ፤
- ስዕላዊ ድርሰትን ትጽፋላችሁ፤
- የቃላትን ቀጥተኛ ትርጉም ትፈልጋላችሁ፤
- ነጠላ ዓረፍተ ነረሮችን ትመሰርታላችሁ፤
- የተለያዩ ተረቶችን ትናገራላችሁ፤
- የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን ድምፀት አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፤
- በጋራ በመሆን በሐገር ፍቅር ዙሪያ ትወያያላችሁ፤

## ሃያ ሶስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰባ አንድ

### ሲጨልም

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- ከአጭር ልቦለዱ ውስጥ ዋና ዋና ገፀባህርያትንና መቼቶችን መለየት፡፡

## ማስታወሻ

- ልቦለድ ማለት በእውነተኛው አለም ያለን አንድ ታሪክ በገፀባህርያት አማካይነት ወክሎ የሚያቀርብ ዝርው(በዓ.ነገሮችና በአንቀጽ የሚዋቀር) የፈጠራ ስራ/የሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡
- አንድ ልቦለድ ሲጻፍ ስምንት መሰረታዊ ነገሮችን መያዝ ይኖርበታል፡፡ ማለትም፡-ታሪክ፣የታሪክ መዋቅር፣ገጸባህርያት፣መቼት፣ቋንቋ፣ግጭት፣ አንጻርና መልዕክትን፤ እንዲሁም ለማዋቀር ወይም ለመፃፍ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ምልልስ፣ምልሰት፣ንግርና ገለጻ ናቸው፡፡
- ሀ.ገፀባህርያት፡- በገሃዱ(በእውነተኛው) ዓለም ያሉትን ሰዎች አጠቃላይ ገጽታና ባህሪ ወክለው በልቦለዱ የቀረቡ የምናብ ዓለም ሰዎች/ውክልናዎች ናቸው፡፡
- ለ.መቼት፡- በልቦለዱ የተቀመጡት ገጸባህርያት የሚኖሩበትና የሚሞቱበት አጠቃላይ የጊዜና የቦታ ሁኔታ ነው፡፡

## ? መልመጃ፡-#9

### ሀ. ቅድመ-ንባብ መልመጃ

1. ከዚህ በፊት ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ስሙን ጥቀሱ፡፡
2. ቀጥሎ የሚቀርብላችሁ አጭር ልቦለድ ምን ምን ሀሳቦችን የሚይዝ ይመስላችኋል?



ወደ ሰባዎቹ የሚጠጉ የሚመስሉ አንድ አረጋዊ "ልጄ" አሉት አስተናጋጁን፤ "የገዛሁህን መድሐኒት ይዤብህ መጣሁ፣እባክህ የሰጠሽኝን ወስደህ..." አላስጨረሳቸውም ግድግዳ ላይ ወደተለጠፈው ጽሑፍ አመለከታቸው፡፡ "የተሸጠ መድሐኒት አይመለስም!" አረጋዊው በለሰለሱ ቃላት መማፀን ያዙ፡፡

"ሰውዬ ዞር በል! ስራ ልስራበት! ለእንቶ ፈንቶ ጉዳይ የማባክነው ጊዜ የለኝም...›› አለ ቁጣው እየተወለደ፤"ዛሬ በዚህ ሰውዬ እንድጨቀጨቅ ተፈርዶብኛል ልበል?›› "እባክህን ልጄ አሳፋሪ ነገር ደርሶብኝ ነው፡፡...ዘመድና ዕድር የሌለኝ ከርታታ ሽማግሌ ስለሆንኩ እንጂ..." አሉት ትሁት በሆነች ፈገግታ ሊያባብሉት እየሞከሩ፤ "ቅናሽ ዋጋ ብትከፍለኝም..."

"ይኼ ሰውዬ ነካ ያደርገዋል ልበል?" አለና ሌሎች መድሐኒት ገዥዎችን ያስተናግድ ገባ፡፡ "ከያዙ አይለቁ"

"ድህነት ቢፈትነኝ ነው ልጄ" አሉ-ያደፈና የነተበ ነጠላቸውን እያሳዩት፡፡ ነጠላቸው ከሰውነታቸው በከፋ ሁኔታ ያረጀ ኮታቸውን ደብቆላቸዋል፤"አቅሜ የደከመ ባይሆን

ኖሮ…” አሉት፤ጫማ ካገኘ የከረመ እግራቸውን እያዩ፡፡

አንዲት አስተናጋጅ “አልመልስም ካለ አልመልስም ነው፡፡ለምንድነው የሚነዘንዙት ?” አለች በሚነጫነጭ ድምጽ፤“ይኼኮ ፋርማሲ እንጂ አዛውንቶች የሚጦሩበት የድኩማን መርጃ ድርጅት አይደለም፡፡” አነጋገሯን ያልወደደው የሚመስል ሌላኛው ጎልማሳ ደግሞ፤“መድሐኒቱን ሙሉ በሙሉ የገዙት ከዚሁ መደብር ነው?” የሚል ጥያቄ አመጣ፡፡

“አዎ፤ዶክተሩ ጽፎ በሰጠኝ መሰረት” ብለው መለሱለት፡፡ “ምን ያህል ፈጀብዎ?” “ሰባ ሁለት ብር ከሰማንያ አምስት ሳንቲም፡፡ መድሀኒቱን ወስዶ ግማሹን እንኳን ቢሰጠኝ ምን አለበት?” አሉ በሃዘኔታ፤“የሁለታችንንም የጋብቻ ቀለበት አስይዤ ነው ከማምነው ሰው የተበደርኩት”

“መድሐኒቱን ለምን መመለስ ፈለጉ?” አሉ፤ ዘንቢል ያንጠለጠሉ አንዲት አሮጊት፡፡ በዚህ ጊዜ አስተናጋጁ ጣልቃ ገባ፤ “ባህላዊ ህክምና ብትከታተል ኪስ እንደማያራቁት ገብቷቸው ይሆናላ! ወይ ፀበል ሊያስጠምቋት!ወይ…” “ኧይ ልጄ! ጉዳዩን ብታውቀው ኖሮ ያፌዝክበት ምላስህን ታፍርበት ነበር…” አሉ እንባ እየተናነቃቸው፡፡ “መድሐኒቱን ምን ላድርገው? ልዋጠው ወይስ ሽንት ቤት ልጨምረው?”

“ለባለቤቴ ነው የገዛሁላት ብለው አልነበር?...በጠና ታማብኛለች፤የእድሜዬ ጀምበር እየጠለቀ ባለበት ሰዓት ለእህል ያላነሱና ለትምህርት ያልደረሱ ሶስት ልጆች በትናብኝ እንዳትሄድ ፀልይልኝ፤ ብለውኝ አልነበር?”

“ማለቱንስ ብዬህ ነበር ልጄ!...ብዬህ ነበር” “እና ሩብ ሰዓት ያህል እንኳን ሳይቆዩ ሀሳብዎን አሰርዞ፤የገዙትን መድኃኒት የሚያስመልስ ምን ተአምር ተፈጠረ?! ቅድም የማይመለከተኝን ነገር ሲዘላብዱብኝ ነበር እኮ” አረጋዊው አንገታቸውን ደፉ፡፡ “እኮ ምን ቢፈጠር ነው…?” “ቤቴ ሳልደርስ ነው አንተ ዘንድ የመጣሁት” “ለምን?” አሉ ሌሎቹ፡፡ “ሰፈርተኞቼ ደጄ ላይ ሲጯጯሁ አየሁ፡፡ ባለቤቴን በሕይወቷ ልደርስላት አልቻልኩም!” አሉ አረጋዊው ድምጻቸው እየሻከረ፤ እንባቸው እየወረደ፡፡ በመድሀኒት ሻጩ ፊት ላይ ፀፀትና ድንጋጤ እየታየ ድፍን መቶ ብር አውጥቶ በሻካራ እጆቻቸው ላይ አኖረ፡፡ ሌሎቹም ኪሶቻቸውን ይፈትሹ ጀመር፡፡ “ይባርካችሁ ልጆቼ! ከፈን መግዣ ስላልነበረኝ እንጂ…” እንባ ተናነቃቸው፡፡ መንሰቅሰቃቸውንም እየቀጠሉ ወጡ፡፡ ፀጥታ!

ምንጭ፡- “ከጥቁር ሰማይ ስር”፣ እንዳለጌታ ከበደ፣2009፣43-45

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ያነበባችሁት አጭር ልቦለድ ጊዜውና ቦታው የት ነው?
2. በልቦለዱ ውስጥ ድርጊቱን የሚያከናውኑት ሰዎች እነማን ናቸው?
3. የቀረበላችሁ አጭር ልቦለድ መልዕክቱ ምንድን ነው?

ሐ. ቀጥለው በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ክፍል የሚስማማቸውን ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. መጨቅጨቅ | ሀ.ሲረብሹ |
| 2. ደብቆላቸው | ለ.እየተነበበ |
| 3. ድኩማን | ሐ.ጥላብኝ |
| 4. ያልወደደው | መ.ያልፈለገው |
| 5. ያንጠለጠሉ | ሠ.የያዙ |
| 6. በትናብኝ | ረ.አቅም ያነሳቸው |
| 7. ሲዘላብዱብኝ | ሰ.መነታረክ |
| 8. ሲጯጯሁ | ሸ.ሸሽጎላቸው |
| 9. እየታየ | ቀ.ሲዘባርቁብኝ |
| 10. ከፈን | በ.ልብስ |
| | ተ.ሲበሉ |

# ክፍለ ትምህርት ሰባ ሁለት

## ድርሰት

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

✅ የድርሰትን ምንነት፣አይነትና አጻጻፍ ዘዴ መለየት፡፡

ድርሰት ማለት በአንድ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መሰረት አድርጎ፣ፈጠራዊ በሆነ አልያም ባልሆነ መንገድ፣በዝርዋዊ(በአንቀጽ ተደራጅቶ) ወይም በግጥማዊ(ምትና

ዜማ ኖሮት) ስልት የሚቀርብ፤የኪነ-ጥበብ ዘውግ ነው፡፡

ድርሰት በአራት ዋና ዋና መደቦች ሊከፈል ይችላል፡፡ይኸውም፡-ተራኪ ድርሰት፣ ስዕላዊ ድርሰት፣አመዛዛኝ ድርሰትና ገላጭ ድርሰት በመባል፡፡ እነዚህ የድርሰት ክፍሎች ተቀራራቢነት ያላቸው ቢመስሉም የተለያዩ ናቸው፡፡

የተዋጣለት ድርሰትን ለመጻፍ የምንከተላቸው ሒደቶች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም፡ - ርዕስ መምርጥ፣ርዕስ ማጥበብ(ማሳጠር)፣ ቢጋር/አስተዋጽኦ መንደፍ፣ ረቂቅ ማውጣት፣ማስተካከያ ማድረግና የመጨረሻውን ጽሑፍ ለንባብ ማብቃት ናቸው፡፡

## ? መልመጃ፡-$

ሀ. ቀጥለው የቀረቡት ጥያቄዎች ከላይ ካለው ምንባብ የተውጣጡ ናቸው፡፡ እንደአጠያየቃቸውም ምላሽ ስጡ፡፡

1. የተዋጣለት ድርሰትን ለማዘጋጀት የምንከተላቸው ቅደም-ተከተሎች ምን ምንድን ናቸው?
2. የድርሰት አይነቶች ስንት ናቸው? ስማቸውንም ጥቀሱ፡፡
3. ድርሰት ምንድን ነው?

ለ.ቀጥለው በ“ሀ” ረድፍ ላሉት በሀሳብ የሚዛመዷቸውን ከ“ለ” ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ስልት | ሀ.ተመሳሳይ |
| 2. ረቂቅ | ለ.ግጥም ያልሆነ ጽሑፍ |
| 3. ዝርው | ሐ.አወዳዳሪ |
| 4. ተቀራራቢ | መ.ፈጠራ |
| 5. ዘውግ | ሠ.አይነት |
| 6. አመዛዛኝ | ረ.ንድፍ |
| | ሰ.ዘዴ |

# ሃያ አራተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰባ ሶስት

### ስዕላዊ ድርሰት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- ስዕላዊ ድርሰትን ማዘጋጀት፡፡

**ተግባር፡-19**

ተማሪዎች! በመጀመሪያ መምህራችሁ የሚያስረዷችሁን በጥሞና በመከታተል፤ አንድ አጠር ያለ ስእላዊ ድርሰትን አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡ በቤታችሁም በመሄድ በሌላ ርዕስ ተለማመዱ፡፡

## ክፍለ ትምህርት ሰባ አራት

### የቃላት ቀጥተኛ ትርጉም

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የቃላትን ቀጥተኛ/መዝገበ ቃላዊ ትርጉም መስጠት፡፡

**? መልመጃ፡-፷፩**

ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት መዝገበ ቃላዊ ትርጉም ፈልጉላቸው፡፡

ምሳሌ፡- አረፈ፡- እረፍት አደረገ፣ሞተ

| | |
|---|---|
| ሀ. ወደቀ | ሠ.ዛላ |
| ለ. ለማ | ረ.ቃና |
| ሐ.ቀመሰ | ሰ.ሻኛ |
| መ.ማማ | |

# ክፍለ ትምህርት ሰባ አምስት

## ነጠላ ዓረፍተ ነገር

### የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ

- ነጠላ ዓ.ነገሮችን መመስረት፡፡

### ማስታወሻ

- ዓ.ነገር ማለት አንድ የተሟላ ሀሳብን የያዘ፤በስማዊ ሐረግና በግሳዊ ሀረግ የሚመሰረት፤በውስጡ ባለቤት፣ተሳቢና ግስን ያቀፈ ነው፡፡
- ዋና ዋና የዓ.ነገር አይነቶች ከሚባሉት መካከል፡- ነጠላና ድርብ ዓ.ነገሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ነጠላ ዓ.ነገሮች አንድ ግስን(ማሰሪያ ዓ.ነገርን) ብቻ የሚይዙ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

-እናቴ ከገበያ ሎሚ፣ቲማቲምና ሽንኩርት ገዛች፡፡

-ዛሬ ወደ አርባ ምንጭ እሄዳለሁ፡፡

## ? መልመጃ፡-$2

ቀጥለው በቀረቡት ቃላት ነጠላ ዓ.ነገሮችን መስርቱባቸው፡፡

1. ጻፈ
2. መጣሁ
3. ሄደ
4. ወጡ
5. ጎበጠ
6. ተኛሁ
7. ለቀሙ
8. ሰነዘረ
9. በላ
10. ጨበጠ

# ሃያ አምስተኛ ሳምንት

## ክፍለ ትምህርት ሰባ ስድስት

### ተረቶችን መናገር

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ:**

- የታሪክ ፍሰቱን የጠበቀ ተረት መናገር።

### ተግባር-20

ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚነገሩ ተረቶችን በመጠየቅ ወይም በልዩ ልዩ መጻሕፍት፣ጋዜጦች፣መጽሄት ወዘተ የሰፈሩትን በመመዝገብ ተለማመዱና በትክክለኛው አቀራረብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።

## ክፍለ ትምህርት ሰባ ሰባት

### የዓረፍተ ነገሮችን ድምጸት ማዳመጥ

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- የዓ.ነገሮችን ድምፀት አዳምጦ መናገር።

### ተግባር-21

ተማሪዎች በቅድሚያ መምህራችሁ የሚሏችሁን መመሪያ ተከታተሉ። ቀጥሎም የሚያስደምጧችሁን ልዩ ልዩ ዓ.ነገሮች ድምፀት ምን ሊሆን እንደሚችል በአንክሮ በመከታተል መልሳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታቀርባላችሁ።

## ክፍለ ትምህርት ሰባ ስምንት

### ውይይት

**የክፍለ ትምህርቱ ንዑስ አላማ**

- በጋራ በመሆን ስለ ሐገር ፍቅር ስሜት መወያየት።

## ተግባር-22

በጋራ በመሆን ቡድን መስርታችሁ ስለሀገር ፍቅር ስሜት ተወያዩና የጋራ ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

# ማጣቀሻዎች


ትምህርት ሚኒስቴር፡፡2004፡፡አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ፣9ኛክፍል፡፡አዲስ አበባ፤ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡2007፡፡አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ፣7ኛእና 8ኛክፍል፡፡ ህንድ፤ፒተምበር ቡክ ማተሚያ ቤት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡2008፡፡አማርኛ እንደ 2ኛቋንቋ ፣አምስተኛ ክፍል፡፡ህንድ፤ ቡርዳ ድራክ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማን አህሎት፡፡1992፡፡ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?አዲስ አበባ፤ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

እንዳለጌታ ከበደ፡፡2009፡፡ከጥቁር ሰማይ ስር፡፡አዲስ አበባ፤እታፍዘር አሳታሚዎች፡፡

የደቡብ ክልል ምክር ቤት፡፡2004፡፡የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፕሮፋይል፡፡አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

የደቡብ ክልል ትምህር ቢሮ፡፡1998፡፡አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣6ኛክፍል፡፡አዲስ አበባ፤ኤች.ዋይ.ኢንተ.ማ.ድ.ኃ.የተ.የግ.ማ፡፡

ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡2004፡፡አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ (እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ) ፣5ኛክፍል፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡2004፡፡የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ (እንደ ሁለተኛ ቋንቋ) ፣6ኛክፍል፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡2004፡፡አማርኛ መማሪያ፣ 8ኛክፍል፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፡፡1994፡፡“ኒው ሲስተማቲክ ቡክ ሲሬስ” አማርኛ ከ7ኛ-10ኛክፍል፡፡ አዲስ አበባ፤ብርሐንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታቸው በለጠ፡፡፡2004፡፡የጥበባት ጉባኤ፡፡አዲስ አበባ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡1992፡፡የስነ-ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ፡፡

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል

ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ